የኢትዮጵያ-ፊንላንድ በግብርና ተኮር የንግድ ልማትን መሠረት ያደረገ የኢኮኖሚ እድገት ፕሮገራም በአማራ ክልል

# የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ማኑዋል



ጥር 2006

ባሕርዳር

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 4 |
| 1.1 የአግሮ ቢግ ፕሮገራም | 4 |
| 1.2 የማኑዋሉ አገልግሎት | 5 |
| 1.3 የማኑዋሉ ወሰን | 5 |
| 2. የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ ዓላማዎች | 5 |
| 2.1 ዓላማ፤አገልግሎትና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግበራት | 5 |
| 2.2 ፈንድ የአፈጻጸም ዘዴ ማጠቃለያ | 7 |
| 3. የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ ፕሮጀክት | 9 |
| 3.1 ለፈንዱ ብቁ የሆኑና ብቁ ያልሆኑ አመልካቾች | 9 |
| 3.2 ፕሮጀክቱን ለመፍቀድ በመሰረታዊነት መሟላት የሚገባቸው ቅደመ ሁኔታዎች | 9 |
| 3.3 ሊፈቀድ የሚችሉ የፕሮጅክት ዓይነቶች | 10 |
| 3.4 የፕሮጀክት ድጋፍ የገንዘብ መጠንና የአመልካቹ የመቀናጆ በጀት ድርሻ | 10 |
| 3.5 የፕሮጀክት ድጋፍ በጀት አከፋፈል | 11 |
| 3.6 የፕሮጀክት ቆይታ ጊዜ | 11 |
| 3.7 ለፈንዱ ብቁ የሆኑን ያለሆኑ ወጪዎች | 11 |
| 3.8 ፈርጀ ብዙ ጉዳች፤ ሥርዓተ ፆታና አካባቢ ጥበቃ | 12 |
| 4. ተቋማዊ አወቃቀር | 13 |
| 4.1 የትግበራ ስልት | 13 |
| 4.2 የፕሮጀክት አሰተዳደር | 13 |
| 4.2.1 በክልል ደረጃ | 13 |
| 4.2.2. በወረዳ ደረጃ | 14 |
| 5. የፕሮጀክት ሃሳብ አቀራረብ ሂደት | 16 |
| 5.1 የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳባ አቀራረብ ግንዛቤ መፍጠርና እንዲቀርብ ጥሪ ማስተላለፍ | 17 |
| 5.2 የቀረበን የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ መመርመርና ማጽደቅ | 17 |
| 5.3 ዝርዝር የፕሮጀክት ሃሰብ አዘገጃጀት | 19 |
| 5.4 ማጽደቅና አመልካቹ ውል እንዲወስድ ማሰወቅ | 20 |

| | |
|---|---|
| 6. የድግፍ ፕሮጀክት ትግበራ | 23 |
| 6.1 ሕጋዊ የውል ስምምነት | 23 |
| 6.2 የባንክ ሂሳብ ቁጥርና የክፍያ አፈፃፀም | 23 |
| 6.3 ግዢ | 24 |
| 6.4 የፋይናንስ አስተዳድርና የሂሳብ አያያዝ | 24 |
| 6.5 የሩብ ዓመት ክንውን ሪፖርት | 24 |
| 6.6 የፋይናንስ ሪፖርት | 24 |
| 6.7 ክትትልና ቁጥጥር | 25 |
| 6.8 የማጠናቀቂያ ሪፖርትና ፕሮጀክትን መዝጋት | 26 |
| 7. የማጠናቀቂያ ሂሳብ ምርመራ (ኦዲት) | 27 |
| 8. የፕሮጀክት ውጤትን መመዘንና የመጣውን አወንታዊ ተፅዕኖ መዳሰስ | 27 |
| አባሪ 1፡ የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሰብ ማቅረቢያ ቅፅ | 30 |
| አባሪ 2፡ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ መገምገሚያ ቅጽ | 32 |
| አባሪ 3፡ የፕሮጀክት ሃሳብ ማቅረቢያ ቅጽ | 33 |
| አባሪ 4፡ ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች መከታተያ ሠንጠረዥ | 35 |
| አባሪ 5፡ የፕሮጀክት ሃሳብ መገምገሚያ ቅፅ | 36 |
| አባሪ 6 ሕጋዊ የበጀት ድጋፍ የውል ስምምነት ቅፅ | 38 |
| አባሪ 7፡ የሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ | 42 |
| አባሪ 8፡ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ | 43 |
| አባሪ 9፡ የበጀት ድጋፍ መጠየቂያ ቅፅ | 44 |
| አባሪ 10፡ የፕሮጅክት ማጠናቀሪያ ሪፖርት ቅፅ | 45 |
| አባሪ 11፡ የቡድን ተኮር ማወያያ ቅፅ | 46 |
| አባሪ 12፡ የተጠቃሚዎችን መስክርነት ማሰባሰብ ቅፅ | 47 |

## 1. መግቢያ

### 1.1 የአግሮ ቢግ ፕሮገራም

አግሮቢግ በኢትዮጵያና በፊንላንድ መግስታት መካከል በተደረገ ስምምነት የግብርናን ምርት ከንግድ ጋር በማተሳሰርና ለማበልጸግ በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አስተባባሪነት የሚተገበር ፕሮገራም ነው፡፡

ዋነኛው የፕሮገራሙ ዓላማ የግበርናን ምርት በማስደግ ድህነትን ለመቀነስ በሚደረግው እርብርብ የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው፡፡

የፕሮገራሙ ግንባር ቀደም ተጠቃሚዎች 1) ፕሮገራሙን ለመተግበር በተመረጡ ወረዳዎች የሚገኙ ድሃ የአርሶ አደር ማህበረሰቦችና አባ/እማወራዎች በተለይ ለድህነት የተጋለጡ የማህበረሰብ ክፈሎች፤ 2/ በግብርና ሥራ የተሰማሩ ማህበራትና አቀነባባሪ ኩባንያዎች እና፤ 3/ የህዝብና የግል ድርጅቶች ሲሆኑ ከፕሮገራሙ የአቅም ግንባታ ተጋበራት ተጠቃሚ ናቸው፡፡

አግሮቢግ የ3 ዓመት ፕሮገራም ሲሆን ቆየታው እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከ2013-2015 ድረስ የሚቆይ ነው፡፡ ፕሮገራሙ በመጀመሪያው ምዕራፍ በሜጫና ፎገራ ወረዳዎች በግበርና የስራ ዘርፍ (ሽንኩርትና ድንች) ላይ የተሰማሩትንና አንስተኛ ባለይዞታዎችን የሚደግፍ ሆኖ በሁለተኛው ምዕራፍ ተጨማሪ ወረዳዎችንና ሌሎች ምርቶችን አካቶ ድጋፉን የማስፋፋት እቅድ ይዟል፡፡

**አግሮቢግ ፕሮገራም ሥራዎችን በ3 ምደቦች ከፍሎ ያከናወናል፡፡**

1. **የእሴት ሰንሰለት ልማት:** የባለድርሻ አካላትን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ የጋራ ግንኙነት እንዲፈጥሩ ማመቻቸት፤ ችግሮች እንዲለዩና መፍትሄያቸውን በጋራ እንዲያስቀምጡ ማገዝ ትርፋማነት የሚገኝበትን ዘዴ ለመፈጸም የጋራ ድርጊት መርሀ ግብር መንድፍ ያጠቃልላል፡፡

2. **የአገልግሎት አሰጣትን ማጎልበት:** በእሴት ሰንሰለት ማበልጸግ ላይ ሚና የሚኖራቸውን ተዋንያን ምርታቸውን እንዲያሳድጉ፤ ንግዳቸውን እንዲያሰፋፉ፤ የማቀነባበር ጉልበታቸው እንዲዳብር፤ የገበያ ትስስራቸው እንዲጠነክርና የአገልገግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሳድጉ የሚደረግ ድግፍ ነው፡፡

3. **የፋይናንስ ተደራሽነት:** ቁጠባንና የብድር አገለግሎትን ማበረታታት፤ የተንቀሳቃሽ (ሞባይል) ባንኪግን በአርሶ ሰደሩ ዘንድ ለማስተዋወቅና ለመተግበር፤ በተመረጡ ምርቶች ላይ ፈጠራን አካቶና የእሴት ሰንሰለቱን የሚያበለጽጉ ጉዳዮች በገነዝብ ለመደገፍ ሲሆን በዚህ ረገድ ፕሮገራሙ 3 የተለያዩ የፋይናንስ አቅረቦት ይኖረዋል፡፡ እነሱም፤-
   - የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ

- የእሴት ሰንሰለት ድጋፍ ፈንድ
- የፈጠራ፤ ሰርቶ ማሳያና የምርምር ድጋፍ ፈንድ ናቸው፡፡

ይህ ማኑዋል የሚያተኩረው በመጀመሪያ ደራጃ ለተጠቀሰው የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ላይ ሲሆን በተከታታይ ለፈጠራ፤ለስረቶማሳያና ምርምር ፈንድ እንዲሁም ለእሴት ሰንሰለት ድጋፍ ፈንድ የየራሳቸው ማኑዋል ይኖራቸዋል፡፡

በአማራ ክልል በግብርና እሴት ሰንሰለት ላይ ድጋፍ የሚያደርጉ ሌሎች አጋር ድርጅቶች አሉ፡፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል (Agricultural Growth Programme, Ethiopian Nile Irigation & Drainage Project, The Rice Value Chain of Mennonite Economic Development Associates). እነዚህ ፕሮጀክቶች ባለፉት ጊዚያት በፈንድ አስተዳደር ያካበቱትን ልምድና ተሞኩሮ አካፈለዋል፡፡ እነዚህ አጋር ድርጅቶች ይንቀሳቀሱበቸው የነበሩ አካባቢዎች፤ ለእሴት ሰንሰለት የተመረጡት ምርቶችና የሚሰጡት ድጋፍ ይለያያል፡፡ ይህን ማኑዋል ለማዘጋጀት ሲባል ይከተሉት በነበረውን ስልትና በማኑዋላቸው ላይ እንዲሁም ወጥ የሆነ አሰራርን ለማስፈንን ድግግሞሽን ለማሰወገድ ጥናት ተደረጓል፡፡

### 1.2 የማኑዋሉ አገልግሎት

የዚህ ማኑዋል አገልግሎት ስለመቃናጀ ድጋፍ ፈንድ ትግበራ በሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘንድ ግለፀኝነትንና ተጠያቂነት በውል እንዲረዱት ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ማኑዋል ፕሮጅክቱ ተጋባራዊ በሚሆኑባቸው ወረዳዎች ውሰጥ ስለፈንዱን ዓላማና መርሆች፡ ተቋማዊ አደረጃጀት፡ በፈንዱ የሚሸፈኑና የፈንዱ ተጠቃሚ ለመሆን ለማመልከት የሚከተሉዋቸውን ሂደቶችንና ይሁንታን ለማግኘት እንዲሁም የክትተለና ምዘና ሂደት አካቶ የያዘ ነው፡፡

ማኑዋሉ ሁሉንም አካላት (ተጠቃሚ ለመሆን የሚያመለክቱትን፤ ፈፃሚ አካላትና የፈንዱን አሰተዳዳሪዎች) በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት ስለሚኖራቸው ሚናና መከትል ሰለሚገባቸው ሂደቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል፡፡

### 1.3 የማኑዋሉ ወሰን

ይህ ማኑዋል በመጀመሪያው አንድ ዓመት ፕሮጅከቱ የሙከራ ዘመን እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ የሙከራ ጊዜም በሚገኘው ተሞክሮ የፈንዱ አስተባባሪ ጽ/ቤት እንዳሰፈላጊነቱ ክለሳ በማደረግ በፕሮገራሙ ሥራ አመራሩ ቦርድ እንዲጸድቅ ያደርጋል፡፡

## 2. የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ዓላማዎች

### 2.1 ዓላማ፤አገልግሎትና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግበራት

**የዚህ ፈንድ ጥቅል ዓላማዎች፡-**

- በተመረጡ ምርቶች ላይ አንስተኛ፤ መካከለኛና ጥቃቅን እንተርፕራይዞችን ወደ ኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ ለመሳብ
- ጥቃቅን፤ አንስተኛና መካከለኛ እንተርፕራይዞች የአንስተኛ አምራቾች ቡድንና ማህበራት በተመረጡ ምርቶች ላይ እሴት እንዲጨምሩ በማገዝ ምርቱ በገበያ ላይ ተፈላጊነቱን ለማሰደግ
- አዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመውሰድ በግል የተሰማሩትን አምራቾች ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በማስተሳሰር የተፋጠነ የግብርና ግብይትን ለማሳደግ
- የግብርና ዘርፍ እንዲያድገ በማገዝ በድህነት ቅነሳ ላይ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡

የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ጠቅል ዓላማው ከላይ ከተገለፀው ይበልጥ ጠለቅ ብሎ አገልግሎት የሚሰጠው ከፍተኛ የኢንቨስትመንት ወጪ በመጠቀም የማቀነባበር ፤ ከድህረ-ምርት ጋር ተያይዞ ሊሚጠይቁ ቴክኖሎጂዎች፤ደረጃውን የጠበቀ መጋዝን ለማዘጋጀት፤ ምርትን በተሸለ ሁኔጣ በማሸግ ለገበያ ለማዘጋጀት፤ ምርቱ የራሱ የሆነ መለያ ስያሜ (ብራንድ) እንዲኖረውና ከገበያ ጋር ለተያያዙ ተግባራት ድጋፍ ለማድረግ ሆኖ

- እሴት ሰንሰለት ማበልጸግ ላይ ለተሰማሩ አካላት በተለይ ከድህረ-ምርት እስከተጠቃሚው ድረስ ለገበያ ለማቅረብ ባለው ሂደት ላይ ፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ
- በግብርና ላይ የተሰማሩ እንተርፕራይዞች በቀላሉ በሌላ የፋይናንስ ምንጭ የግብርና ግብይት ፕሮጅክት ለማከናወን የሚቸገሩበትንና ከዚህ በፊት በክልሉ ተሞክሮ የማያውቀውን በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ስልት በመታገዝ የአመራረት ዘዴያቸውን በማሳደግ ተጠቃሚ ለማደርግ፤
- አንስተኛ አምራቾች በተለይም የግብርና ገበያ ተኮር የሆኑትን ምርጥ ተሞክሮዎችንና ስልቶችን እንዲወስዱ መደገፍ፤ አምራቾችና ነጋዴዎች የንግድ ትስስር እንዲፈጥሩ ማመቻቸት፤ በአምራቾችና በግብርና ምርቶች አቀነባባሪዎች መካከል ትስስር በመፈጠር በምርቱ ላይ እሴት በመጨመር የገበያ እድል መክፈት
- አዲስ ምርቶችን ለማምረት የመነሻ ካፒታል መደገፍ፤ ጥሩ የግብርና ተሞክሮዎችን እንዲወስዱ ማገዝ፤ በእሴት ስንሰለት አማካኝነት የታሻሻለና ደረጃዉን የጠበቀ የምግብ ዋሰትና መጠበቅ፤ የድህረ ምርት እንክብካቤና መልካም አያያዝ እንዲኖር ማገዝ፤ ገበያ ተኮር የሆነ የምርት አሰተሸሻግ፤የምረቱ ልዩ መለያ ለመሰየም /ብራንድ መስጠት/ አመች የትራንሰፖርት አገልግሎትና ዘመናዊ የመረጃ ለውውጥ እንዲኖር ማገዝ፤ ኮንተራከታዊ የግበርና ዘዴ እንዲመሰረትና ጥራቱን የጠበቀና ለገበያ የሚቀርብ የግብርና ምርት እንዲኖር መደገፍ፡፡
- ከባንክ ጋር ሊተሳሰር የሚችል የንግድ ልማት እቅድ ማዘጋጀት፤ በመሆኑም ጥቃቅን፤ አንስተኛና መካከለኛ እንተርፕራይዞች የፋይናንስ ችግራቸውን ወደፊተ ከአበዳሪ የፋናንስ ተቋማት ጋር በማሰተሳሰር እንዲፈቱ ማገዝ የሚሉት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

ቅደሚያ የሚሰጣቸው የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ተግባራት ፕሮጅክቱ በሚተገበርባቸው አካባቢዎች የተመረጡ የግብርና ምርቶች ላይ ነው፡፡

- ለተመረጡ የገበርና ምርቶች እሴት ሰንሰለት  ልማት የፋይናንስ ድጋፍ ማደረግ፤ በአግሮ ቢግ ፕሮገራም  ለመጀመሪያ ጊዜ ሽንኩረትና ድንች የተመረጡ ሲሆን የእሴት ሰንሰለት ተግባር በእነዚህ ምርቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በቀጣይነት ሌሎች ምርቶች ሊካተቱ ይችላል፡፡
- በእነዚህ ምርቶች ላይ አተኩሮ የሚሰሩ  የሰራ ፈጣሪዎችና እንዱስትሪዎች ሲሆኑ የፀደቀ የንግድ ልማተ ቅድ ሲያቀርቡ ከፕሮጀክቱ የሚሰጠውን የመቀናጀ የፋይናንስ ድጋፍ ያገኛሉ፡፡
- የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ለመጠቀም ያታና ፍታሃዊነት ዋነኞቹ የመሠረት ድንጋይ ሲሆኑ ሴቶችና ከሃብት አንፃር ወደጎን የተገለሉ ወገኖች ከዚህ ፕሮገራም ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## 2.2 ፈንድ የአፈጻጸም ዘዴ ማጠቃለያ

ከዚህ በታች የተመለከተው ሠንጠረዥ ስለ መቀናጀ ድጋፍ ፈንድ አጠቃላይ ገፅታ ያስረዳል፡፡ ዝርዝር መረጃ  ዕራፍ 3 ተካቷል፡፡

| | የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ |
|---|---|
| አገልገሎት | ሰፋፊ እንቨስትመንቶችን ለማስፋፋት<br>• የማቀነባበር፤ የምርት መጠን፤ የማሸግ ፤ የማከማቻና ስርጭትን አቅም ለማሳደግ<br>• በከፍተኛ ደረጃ በተመረጡ የእሴት ሰንሰለት ላይ የሚያተኩር |
| ዓይነት | በፕሮገራሙ በሚቀርብ ድጋፍ፤ የአመልካቹ መዋጮና ብድር |
| ሊሰጥ የሚችል ከፍተኛው የፋይናንስ ድጋፍ መጠን | ለአንድ ተግባር ከፍተኛው እስከ 2,600,000 ብር ዝቅተኛው ከ52,000 ብር ድረስ |
| የክፍያ አፈፃጸም | የተከናወነው ተግባር አፈፃፀም  አየተለካ<br>የማጠናቀቂያ ሪፖርት ሲቀርብ |
| ገዢ ነገር | የተፈቀደ የፕሮጅክት ሃሳብ ማመልከቻና የጸደቀ የንግድ ልማት እቅድ እቅድ |
| የፋይናንስ ድጋፍ አወቃቀር | |

| | |
|---|---|
| **የራስ መዋጮ ድርሻ** | ጠያቂው የአጠቃላይ ወጪዉን ቢያንስ 50% ድርስ በራሱ መሸፈን ይጠበቅበታል |
| **የተጠቃሚዎች ቅድመ ሁኔታዎች** | 1. የተመዘገቡና ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ተቋማት<br>2. ሥራው የሚከናወነው በአማራ ክልል ሆኖ ከፕሮጅከት ወረዳዎች ከ100 ኪ/ሜ የማይርቅና የእሴት ሰንሰለቱን በጥሩ ሁኔታ የሚያግዙ |
| **በመሠረታዊነት መዋለ ነዋይን ኢንቨስት ለማደርገ የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች** | 3. በተመረጡ የግበርና ምርቶች ሆኖ ኢንቨስተመንቱ እሴት መጨር ይኖረበታለ<br>4. በፋይናንስም ሆነ በቴክኒክ አዋጭነት ያለው<br>5. ዘላቂነት ያለው የአካባቢ ጥበቃን የሚያበራታታ<br>6. በውስጡ አዲስ ቴክኖሎጂና ምርጥ ተሞክሮዎችን ያካተተ<br>7. የገበያ አዋጭነቱ አስተማማኝነቱ በትንታኔ የታገዘ<br>8. ለምርቱ ወይም ለአገለግሎቱ አስተማማኝ ገበያ ስለመኖሩ የተረጋገጠ |
| **ልዩ ቅድመ ሁኔታ** | 9. የእሴት ሰንሰለት ትግብራ ከድሃ አርሶ አደሮች ጋር የተሳሰረ ስለመሆኑ<br>10. የሴቶችን ተሳትፎ የሚያበረታታ ስለመሆኑ |

### 3. የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ፕሮጀክት

### 3.1 ለፈንዱ ብቁ የሆኑና ብቁ ያልሆኑ አመልካቾች

የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ለመጠቀም ብቁ የሆኑ አመልካቾች

ሀ. ጥቃቅን፤ አንስተኛና መካከለኛን እንዲስቱሪዎች ማህበራትና ሌሎች በግብርና የተሰማሩ እንተርፐራይዞች መሆን አለባቸው

ለ. በእሴት ሰንሰለት አገልግሎት የተሰማሩ የግብርና ደላሎች ነጋዴዎች አንስተኛ አቀነባባሪዎች

ሐ. በህበረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ፤ በአንስተኛና ጥቃቅን እንተርፐራይዝ ልማት ኤጀነሲ ወይም በሌላ የመንግስት አካል የትመዘገቡ

መ. ሥራው የሚከናወነው በአማራ ክልል ሆኖ ከፕሮጅከት ወረዳዎች ከ100 ኪ/ሜ የማይርቅና የእሴት ሰንሰለቱን በጥሩ ሁኔታ የሚያግዙ

የአመልካቹ ድርጅት ተወካይ የሆነ ሆኖም አግሮቢግ ፕሮገራም ባዋቀረው ኮሚቴ ውሰጥ አባል ሆኖ የሚቀርቡ የፕሮጀከት ሃሳቦችን የሚገምግም ባለበት ሁኔታ ለዚህ የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ለመጠቀም በቁ አያደርገውም፡፡

### 3.2 ፕሮጀክቱን ለመፍቀድ በመሰረታዊነት መሟላት የሚገባቸው ቅደመ ሁኔታዎች

አመልካቾች ሊያከናዉኑ ያሰቡትን የሥራ እቅዳቸውን በተዘጋጀው የማመልከቻ ሥነስርዓት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሁሉም የሚፈቀዱ የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ የሚከተሉትን ቅድመሁኔታዎች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

- የፕሮጀክቱ ሃሳብ በተመረጡ ምርቶች ላይ እሴት የሚጨምር መሆን አለበት
- በፋይናንስና በቴክኒክ አዋጭ መሆን አለበት
- ዘላቂነት ያለው የአካባቢ እንክብካቤን የሚያበራታታ
- በውስጡ አዲስ ቴክኖሎጂና ምርጥ ተሞክሮዎች የያዘ
- የገበያ አዋጭነቱ በትንታኔ የታገዘ
- የሚመረተው ምርት ወይም አገልገሎት ጥሩ ገበያ ስለመኖሩና ትርፋማ መሆኑ
- ፕሮጀክቱ አንስተኛ ባለይዞታዎችን ከእሴት ሰንሰለት ጋር የሚያሰተሳስርና የሴቶችን ተሳተፎ ስለማበራታቱ መረጋገጥ አለበት፡፡

### 3.3 ሊፈቀድ የሚችሉ የፕሮጅክት ዓይነቶች

በርካታ የተለያዩ የመቀናጀ ድጋፍ የፕሮጀክት ዓይነቶች ሊተገበሩ ይችላሉ፡፡ ለአብነት ያህልም የሚከተሉት የፕሮጀክት ሃሰቦች ባላቸው የንግድ ልማት እቅድ መነሻነት በከፍተኛ ኢንቨስትመንት ወጪ የሚጠይቁ ፕሮጀከቶች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

በቴክኖሎጂ ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤ እሴት ለሚጨምር የማቀነባበሪያ  ማሽነሪ ለምሳሌ

- ከድህረ-ምረት በኋላ ምርቱ ጥራቱን ጠብቆ እንዲቆይ ለሚያግዘህ ማከማቻ መጋዘን (ብክነትን ለመቀነስ፤ ምርቱ ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ ለማቆት)
- የምርቱን ጥራት ለመጠበቅ እንዲያስችል ልየታ ለማደርግ፤ ደረጃ መስጠት
- ምርቱ ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ እንዲቆይ የሚረዳ የማሸጊያ ቴክኖሎጂ፤
- የጅምላና የችርቻሮ ግዢና ሽያጭን ለመመስረት
- ምርቱን ለማጓጓዝና ለማስራጨት ለማስፋፋት የሚረዱ ተግባራት
- ሴቶችና ወጣቶች እሴት በመጨምና በማቀነባበር ረገድ እንዲሳተፉ ለሚያግዙ
- የተለያዩ የአርሶ አደር አደረጃጀትን ከእሴት ሰነሰለት ተዋንያን ጋር ለማስተሳሰር

### 3.4 የፕሮጀክት ድጋፍ የገንዘብ መጠንና የአመልካቹ የመቀናጆ በጀት ድርሻ

የመቀናጆ  ድጋፍ ፈንድ ከዚህ በታች በተመለከተው የተወሰነ ነው፡፡

- **ከፍተኛው የድጋፍ ገንዘብ መጠን** ለአንድ ፕሮጀክት 100,000 ሺ.ህ  ዩሮ (በኢትዮጵያ ብር 2,600,000 ሲሆን ይህም 1 ዩሮ 26 ብር የተሰላ ነው)

- **ዝቅተኛው የገንዘብ መጠን** ለአንድ ተገባር 2,000 ሺ.ህ ዩሮ (52,000 ብር) ነው፡፡

ሁሉም የእሴት ሰንሰለት ፕሮጀክት ሃሳቦች ለወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ መቅረብ የሚገባቸው ሲሆን ኮሚቴው በማወዳደሪያ መስፈርት አወዳድሮና ለፕሮጀክቱ የሚወጣውን ወጪና ከፕሮጅከቱ ትግበራ በኋላ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም አመዛዝኖ ውሳኔ ሃሳብ ያሳርፋል፡፡

**አመልካቾች የፕሮክቱን አጠቃላይ ወጪ ቢያነስ** 50% የመቀናጆ ገንዘብ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመቀናጆ ገንዝብ መጠን በፕሮጀክት ድጋፍ አጽዳቂ ኮሚቴ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ባህሪና ወደፊት ሊገኝ ከሚችለው ውጤት አንጻር  በተናጠል የሚወሰን ይሆናል፡፡

የመቀናጆው ገንዝብ ድርሻ  በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም በሚከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር **በጥሬ ገንዘብ** የፕሮጅክት ድጋፍ ገንዝብ ከመከፈሉ በፊት ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ከማሕበራት፤ ከአንስተኛ የብድር ተቋምና ከንግድ ባንክ የሚገኝ ብድር ለዚሁ የመቀናጆ የፋይናንስ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

### 3.5 የፕሮጀክት ድጋፍ በጀት አከፋፈል

የፕሮጀክቱ ድጋፍ ገንዘብ በፈንዱ ሴክረታሪያት አማካኝነት በቅደሚያ ክፍያና ተከታታይ ክፍያዎች አፈጻጸሙ እየተፈተሸ የሚለቀቅ ይሆናል። የፕሮጀክቱ ሃሳብ በሚዘጋጅበት ወቅት በየጊዜው የሚያስፈለገው የገንዘብ መጠን ከፕሮክቱ ክንዉን ጋር ተጣጥሞ ተካቶ መቅረብ አለበት።

### 3.6 የፕሮጀክት ቆይታ ጊዜ

የፕሮጀክቱ ቆይታ ጊዜ እንደ ፕሮጀክቱ ባህሪ እየታየ በተናጠል የሚወሰን ይሆናል። ሆኖም ግን ፈፃሚ አካላት በዚህ የፕሮጀክት ሙከራ ጊዜ የሚያከናወኑትን ተግባር ከግባቸው ለመድረስ ቢበዛ በአንድ ዓመት ጊዜ ውሰጥ የሚጠናቀቅ ቢሆን ይመረጣል።

### 3.7 ለፈንዱ ብቁ የሆኑን ያለሆኑ ወጪዎች

ለፕሮጀክቱ ብቁ የሆኑ ወጪዎች በሥራ ዕቅዱ ውስጥ የተካተቱት ብቻ ይሆናሉ። በትግበራ ጊዜ የሚወጡ ወጪዎች ሁሉ ለእሴት ሰንሰለት ለማበልፀግ ከተቀመጡት ዓላማዎች አንፃር ያበረከቱት አሰተወፀዖና አሳማኝነቱ በግልጽ ማመላከት አለባቸው። ለአብነት ያህል የወጪ አመዳደቦች ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ሊዋቀሩ ይችላሉ።

- ለመጋዘን ወይም ለማቀነባበሪያ ግንባታ ወይም ዕድሳት (የህንጻውን ወለል፤ግድግዳ፤ወይም ጣሪያ ለማሻሻል ፤ የአየር ማስተንፈሻ ለማዘጋጀት፤ የጥበቃ፤ ኤሎትሪክ ሃይል ለማስገባት)
- ለድህረ-ምርት መያዣ መሳሪያዎች ገዢ፤ ደረጃ ማሳደጊያ፤ ተከላ / ለምሳሌ ማድረቂያ፤ ማፅጃ፤ ማሸጊያ፤ ደረጃ ለማወጣት፤ ለመለየት፤ ፀረ-ተባይና በሽተታን ለሚከላለክል መሳሪያ ግዢ፤ ለሃይል ተከላ
- የማቀነባበሪያ መሳሪያ መግዣ፤ ደረጃ ማሰደጊያ / ለምሳሌ፡ ለመፍጫ፤ማቀላቀያ፤ የተባይና የበሽታ መቆጣጠሪያ መሳሪያ፤ ኤሌትሪክ ለማስገባት .../
- ለአንስተኛ መሳሪያዎች ምገዣ /ሚዛን፤ የሙቀት መለኪያ፤ የሂሳብ መኪናዎች የምርት መደርደሪያ

#### ብቁ ያለሆኑና በዚህ ፈንድ ሊሸፈኑ የማይችሉ ወጪዎች

የዚህ ዓይነት ወጪዎች በእሴት ሰንሰለት ፈንድ ሊሰተናገዱ ስለማችሉ አመልካቹ በራሱ የፋይናንስ ምንጭ የሚሸኑ ይሆናል። እነዚህ ወጪዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ።

- የድርጅቱ የዕለት ከዕለት ወጪዎች (የቀን ስራተኛ የጉለበት ዋጋ ፤ መጓጓዣ/የመኪናና የሞተር ሳይክል)፤ ነዳጅ፤ የኤሌትሪክና የውሃ ፍጆታ፤ ለአላቂ እቃዎች፤ የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህ በአብቁተ በብድር ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው።
- ከተፈቀደው የድጋፍ ፈንድ በቀጥታ ተዛማጅነት የሌላቸው ወጪዎች፡ በውል ስምምነት ላይ ያልተካተቱ ተግባራት ወይም ከፕሮጀክቱ ጋር የማይገናኝ የስልጠና ወጪ
- ከፍተኛ ካፒታል ወጪ የሚጠይቁ መሣሪያዎች እንደ ትልቅ የመስክ ማሽነሪዎች፤ የግንባታ መሣሪያዎች፤ ተሽከረካሪዎች፤ ሰፊ የማቀነባባሪያ የማከማቻ መሣሪያዎች፤

የግንባታ ሥራዎች (ህንፃ፣ ድልድይና መንገድ) የመሬት ግዢ፣ ከህግ ጋር የተያያዙ ወጪዎች

- የውል ስምምነት ከመፈረሙ በፊት የወጡ ወጪዎች መሸፈን፣ የዕዳ መካካሻ፣ አስቀድሞ በሌላ የፋይናንስ ምንጭ የተሸፈነን የማተካካት
- የመንግስትን የዕለት ከዕለት አስተዳዳራዊ ወጪዎች ለመሸፈን
- በፋይናንስ ተቋማት በመሳተፍ አክሲዮን መገዛት
- የምግብና የሆቴል ወጪዎች፣ ስበሰባዎችን ለመሳተፍ የሚከፈል ወጪ ወይም ሥጦታ መስጠት
- ከፕሮጀክቱ ጋር ባልተዛመደ ሁኔታ ለደረሰ ጉዳት ማካካሻ የካሳ ክፍያ በአደራዳሪዎች፣ በስምምነት ወይም በሌሎች ሁኔታዎች ቢወሰንም

## 3.8 ፈርጀ ብዙ ጉዳች፣ ሥርዓተ ፆታና አካባቢ ጥበቃ

ፈርጀ ብዙ ጉዮች በልማት ተግባራት ላይ ተጽዕኖ ስለሚያስድሩ ልዩ የፖሊሲ አቅጣጫ ስለሚያስፈልጋቸው  በዓለም አቀፍ ደረጃ አገሮች በእነዚህ ፖሊሲዎች ላይ አጠቃላይ ስምምነት ደርሰዋል፡፡ የጾታ እኩልነትና የአካባቢ ጥበቃ በፕሮጀክት እቅድና ትግበራ ወቅት ትልቅ ተኩረት ከሚሹ ጉዳች በወነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### <u>ሥርዓተ-ጾታ</u>

የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ በዋነናነት ከያዛቸው ግቦች መካከል በሴቶችና ወንዶችን መካከል  አኩል የሆነ መብት፣ የስራ እድልና ግዴታ እንዲኖር ያበረታታል፡፡  ሴቶች በኢትዮጵያ  በግብርና ዘርፍ በሰፊው ተሰማሪትው እንደመገኘታቸው መጠን  በዚህ የፈይናንስ ድጋፍ ዋነኛ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡ ስለሆነም፣-

- ፕሮጀክቱን ከሚተገብሩት የሴቶች አደረጃጀት፣ ማህበራት ወይም ጥቃቅን ተቋማት ከያዟቸው አባለት መካከል  ሴቶች ድረሻ ቢያነስ 30%  እንደሚሆኑ
- አግሮ ቢግ ፈንድ በመወሰን ረገድ ሲቶች ቢያንስ 40% ሚና እንዲኖራቸው
- በሚቀረጸው የድርጊት መርሃ-ግብር የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በወሳኛነት መካተት ያለበት ሲሆን ለአብነት ያህልም የሴቶች የሥራ ጫና፣ የሃብት ባለቤትነት፣ በአመራረር ጥብብ ስለጠናና የመደራድር ሃይል የመሳሰሉት  ወዘተ... ግምት ውስጥ መግበት ይኖርበታል፡፡
- የሴቶች የሥራ ፈጠራ ለማበረታታት ሲባል የአቅም ግንባታ ተኮር የሆነ ስራዎች የሚከናወኑ ሲሆን የሴቶች አደረጃጀት የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድን ለዚሁ ተግበር እንዲያመለክቱ ይጠበቃል፡፡
- ሴቶችና ተጠቃሚ ያለሆኑ የህብረተሰብ ክፈሎች በዚህ የድጋፍ ፈንድ ተጠቃሚ ለመሆን የፕሮጀክት ሃሳብ እንዲያቀርቡ የሚደገፉ ሲሆን ፕሮጀክቱም በኢኮኖሚና

ማህበራዊ ጉዳች ላይ ዘላቂነት ያለው የመልካም አስተዳደር፤ የፋይናንስ አቅም፤ የስራ እድል፤ ገበያ ተኮርና ትርፋማነትን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡፡

<u>**የአካባቢ ጥበቃ**</u>

የመቀናጀ ድጋፍ ፕሮጀክት ሲተገበር የተፈጥሮ ሃበትንና የአካባቢ ንበረት ከሚያዛባና ከሚጎዳ ጉዳይ ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠይቃል፡፡ የሚቀርቡትን የፕሮጀክት ሃሳቦች ሲመረጡ በተፈጥሮ ሀብትና በህዝብ ላይ ጉዳት አለማደርሰ የሚለውን መርህ የተከተለ መሆን አለበት፡፡ ይህም በማህበረሰቡና በስራው ላይ በሚሰማረው ግለሰብ ዘንድ ሊያደርስ የሚችለውን ችግር ማስወገድ ወይም መቀነስ ያሰችላል፡፡

የሚቀርበውን የፕሮጀክት ሃሰብ የሚመረምሩ አካለት ፈርጀ ብዙ ጉዳችን የሚከታተሉበት ዝርዝር አባሪ 4 ከዚህ ማኑዋል ጋር ተያይዟል፡፡

## 4. ተቋማዊ አወቃቀር

### 4.1 የትግበራ ስልት

በወረዳ ደረጃ ከእሴት ሰንሰለት ጋር በተያያዘ እጥሮቶችን በመለየትና እጥረቶችን ለማስወገድ የሚቀረጹ የመፍተሄ መርሀገብሮችን በመንደፍ ሂደት የመሪ ሚና ይኖረዋል፡፡ የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ተገባራዊ የሚሆነው በውል ለተለዩ ጉዳች ላይ ብቻ ነው፡፡

### 4.2 የፕሮጀክት አሰተዳደር

በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢፌዲሪ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርና የፊንላንድ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር በመንግስታት መካከል የተፈራረሙ ሲሆን በአጠቃለይ በፕሮገራሙ ላይ ስልጣን አላቸው፡፡

#### 4.2.1 በክልል ደረጃ

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሰት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በክልል ደረጃ የአግሮቢግ ፕሮገራም የፈተፈራረመ ሲሆን ፕሮግራሙን የመምራት ሃላፊነት አለው፡፡

**የአግሮ ቢግ የሥራ አመራር ቦርድ**

የሥራ አመራር ቦርዱ ፕሮገራሙን በተመለከተ ስትራቴጂካዊ የመጨረሻና ከፍተኛ ውሳኔዎችን የሚሰጥ አካል ነው፡፡ ቦርዱ በአመት ከ1-2 ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ የቦርዱ አባለትም ገ/ኢ/ል/ሚ/ር፤ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ ቢሮ፤ ከግብርና ቢሮ፤ ከግድና ተራንስፖርት ቢሮ፤ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ፤አ/ብ/ቁ/ተ/፤ የግል ተቋማት ተወካይ እና ከፊንላንድ መንግስት ውጭ ጉዳይ ሚ/ር (ኢምባሲ) በተወከሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት የሚመራ ነው፡፡

### የአግሮቢግ ክልላዊ የቴክኒክ ኮሚቴ

ኮሚቴው በየወሩ የሚሰበሰብ ሲሆን ፕሮገራሙ በአገባቡ መተግበሩን፤ ውጤት መገኘቱንና የፕሮገራሙ ገንዘብ በብቃትና ውጤታማ በሆነ መልኩ መዋሉነን ያረጋግጣል፡፡ ለፕሮገራሙም የቴክኒክ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ የኮሚቴው አባለታም ገ/ኢ/ል/ቢሮ ም/ሃላፊ ሰበሳቢ ሲሆን ግብርና ቢሮ፤ ንግድና ትራነስፖርት ቢሮ፤ እንዱስተሪና ከተማ ልማት፤ የህበረት ሥራ ማስፋፊያ ኤጀንሲ፤ የአማራ ነጋዴ ሴቶች ማህበር፤ የአማራ ንግድ መ/ቤትና ዘርፍ ማህበራት ፤ ቴክኒክና ሙያ ቢሮ፤ አብቁተና አግሮ ቢግ (ፀሃፊ) ሆኖ የተዋቀረ ነው፡፡

### የፈንድ ሴክረታሪያት

የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድን በክልል ደረጃ የማስተዳደሩ ሃላፊነት የክልሉ ገ/ኢ/ል/ቢሮ ሲሆን ቢሮው የፈንዱን የዕለተ ከዕለት ተገባር ለማከናወን ለአግሮ ቢግ ፕየሮገራም ድጋፍ ዩኒት ውክልና ይሰጣል፡፡ ዩኒቱም የፕሮገራሙ ጸሃፊ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን በገ/ኢ/ል/ ቢሮ በሚሰየም የፕሮገራም ዳይሬክተርና የቴክኒክ አማካሪ ቡድን በሚመራ የውጭ አለምአቀፍ ቡድን መሪ ይመራል፡፡

የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድን በተመለከተ ማንኛውም ጉዳይ ለፈንዱ ሴክክረታሪያት መላክ የሚቻል ሲሆን ጉዳዩ ለሚመለከተው የክልል ወይም ወረዳ ኮሚቴ እንዲመለከተው ሊመራው ይችላል፡፡

### 4.2.2. በወረዳ ደረጃ

የአግሮቢግ ፕሮገራም በሚተገበርባቸው ወረዳዎች የተለያዩ ኮሚቴዎች ይዋቀራሉ፡፡

### የወረዳ ስቲሪንግ ኮሚቴ

ስቲሪንግ ኮሚቴው በወረዳ አስተዳዳሪ የሚመራ ሆኖ በየሩብ ዓመቱ የሚሰበሰብ ሲሆን በመሃል አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም እንደሁኔታው ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ የኮሚቴው አባላትም የገ/ፕ/ጽ/ቤት

ሃላፊ፤ የግብርና ጽ/ቤት ሃላፊ፤ የንግድና ትራንነስፖርት ጽ/ቤት ሃላፊ፤ የገበሬዎች ማህበራት ዩኒዬን ሃላፊ፤ በአካባቢው የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) እና ሁለት የግል ዘርፍ ተወካዮች ይሆናሉ።

ኮሚቴው የፕሮገራሙን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ፤ በጀትና የክንውን ሪፖርት ያጸድቃል ይመረምራል፤ ፈርጀ ብዙ ሲክተሮችን ያስተባብራል። በወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ ታይቶ የሚመጣለትን የመቀናጀ ድጋፍ የፕሮጀከት ሃሳብ ተቀበሎ ያጸድቃል። ይህን የፋይናንስ ምንጭ ለመጠቀም የሚቀርቡ የፕሮጀክት ሃሳቦች ጥሪ በምን መልኩ መተላለፍ እንዳለበት ይወስናል። በክልል ደረጃ ውሳኔ የሚሹትን ጉዳዮች አይቶ ያስተላለፋል።

**የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ**

ይህ ኮሚቴ ለወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ ሙያዊ ምክር የሚሰጥ ሲሆን በየወሩ እየተሰበሰበ የሚቀርቡትን የመቀናጀ ድጋፍ የፕሮጀክተ ሃሳቦችን እየገመገመና የራሱን ምክረ-ሃሰብ አካቶ ለወረዳው ስቲሪንግ ኮሚቴ ያቀርባል። ኮሚቴው በገ/ፐ/ጽ/ቤት ሃላፊ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ አባላቱም የገ/ፐ/ጽ/ቤት ሙያተኛ፤ የግብርና ጽ/ቤት ተወካይ፤ የንግድና ተራንስፖርት ጽ/ቤት ተወካይ፤ የገበሬዎች ማህበራት ዩኒዬን ተወካይ፤ በአካባቢው የሚገኙ መንግስታዊ ያለሆኑ ድርጅቶች ተወካይ፤ የግል ዘርፍ ተወካዮች፤ የአግሮ ቢግ የወረዳ አስተባበሪና የገ/ፐ/ጽ/ቤት የፋይናንስ ኦፊስር በኮሚቴው ይሳተፋሉ። እንደአስፈላጊነቱ የዞን ገ/ኢ/ል/ ሙያተኛ በኮሚቴው ሊገኝ ይችላል።

**የወረዳ እሴት ሰንሰለት ፈንድ ባለድርሻ አካላት**

በእያንዳንዱ ምርት የተቋቋመው የወረዳ የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ባለድርሻ አካላት በየሩብ ዓመቱ የሚሰበሰብ ሲሆን የግብርና ጽ/ቤት ሰበሳቢነትና በአግሮቢግ ወረዳ አስተባበሪ በመታገዝ ይመራል። ተሰብሳቢዎች በሚገናኙበት ጊዜ በዋጋ ሰንሰለት ማበልጸግ ባሉ ችግሮችና እጥረቶችን ለመቅረፍ በሚወስዱ የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ይወያያል፤ ሊያከናውኑ ያሰቡትንም የድርጊት መርሃ-ግብር ያዘጋጃሉ።

<u>**የወረዳ ፈንድ ሴክረታሪ**</u>

የአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ የፕሮጀከት ሃሳብ ሊያቀርቡ የሚችሉትን አካላት ለመጋበዝ የሚደረግ ጥሪን ያስተባብራል ያመቻቻል። አስተባባሪው የፕሮጀክት ሃሳብ የሚያቀርቡትን አመልካቾች ከወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በመሆን እንዴት መጻፍ እዳለበት እገዛ ያደርጋሉ። ከዚህ በተጨማሪ የወረዳው አግሮቢግ አስተባባሪ የሚከተሉትን ተግባራት የከናውናል።

- ከወረዳ ባለድርሻ አካላት በመሆን የፕሮጀክት ሃሳብ አቀራረብና የአፈቃቀድ ሂደት ያስረዳል ያሳያል፤
- የተዘጋጀውን የድጋፍ ፈንድ በማስተዋወቅ ረገድ የወረዳውን ኮሚቴ ያግዛል ለምሳሌ ሥለ ፕሮጀክት ሃሳብ አቀራረብ ለሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ መፈጠር
- የፕሮጀክት ሃሳበ ያቀረቡ አካላትና የፕሮጀክት ሃሳቦችን መረጃ ይይዛል
- ሊቀርቡ የሚችሉ የፕሮጀክት ሃሰቦችን ያሰረዳል የመስክ ጉብኝት የመቻቻል
- ለአመልካቾች የኮሚቴውን ውሳኔ ያሳውቃል፤ ስለ መቀናጆ ድጋፍ ፈንድ የሚያስፈልጉ ቅደመ ሁኔታዎችና ስለዋናው የፕሮጀክት ሃሳብ አቀራረብ ስለጠና ይሰጣል
- የቀረቡ የፕሮጀክት ሃሳቦች በሙያተኛ እንዲገመገሙ ያደረጋል
- ተቀባይነት ያገኑ የፕሮጀክት ሃሰቦችን የሚያውቁበትን ሁኔታ ያመቻቻል
- ከተመረጡ አመልካቾች ጋር ውል እንዲፈረም ያስተባብራል፤ በውሉ መሰረት ክፍያ መፈፀሙን ይከታላል፤
- የፕሮጀክት ክትትልና ምዘና እንዲካሄድ ያደርጋል

## 5. የፕሮጀክት ሃሳብ አቀራረብ ሂደት

አምለካቾች የፕሮጀክት ሃሳባቸውን በሚያቀርቡት ወቅት በሚያገኙት ገንዝብ በመጠቀም እንዴት እንደሚተገብሩት ዝርዝር የድርጊት መርሃ-ግብር ማያያዝ ያለባቸው ሲሆን ሁለት ቅደም ተከተሎችን መከተል ይጠበቅባቸዋል። በመጀመሪያ አጠር ባለመልኩ የፕሮጀክቱን ንድፈ-ሀሳብ ማቀረብ ሲሆን ጽንሰ-ሃሰቡ በገምጋሚው አካል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑ ሲገጽላቸው ወደ ዝርዝር የፕሮጀክት ሃሳብ ዝግጅት የሚገቡበት ይሆናል። ይህ አሰራር ለማዘጋጀት የሚወስደውን ረጅም ጊዜና ወጪ ለመቀነስ ያግዛል ተብሎ ታስቦ ሲሆን የፕሮጀክት ሃሳቡም በጥራት እንዲቀርብ ሚና ይኖረዋል።

**ቋንቋ**

የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳቡም ሆነ ዝርዝር የፕሮጀክት ሃሳብ በአማርኛ ወይም በእንገሊዘኛ ሊቀርብ ይችላል። የአግሮቢግ ሴክረታሪያት ጽ/ቤት ከመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ ጋር የተያያዙ ሁሉንም መረጃዎች በአማርኛ እንዲወጡ ያደርጋል። ሁሉም የአማርኛ የፕሮጀክት ሃሳቦችና የኮሚቴ ስበሰባ ቃለ-ጉበኤዎች ለመረጃ ሲባል ወደ እንግሊዘኛ የመለሳሉ።

## 5.1 የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳባ አቀራረብ  ግንዛቤ መፍጠርና እንዲቀርብ ጥሪ ማስተላለፍ

በወረዳው የእሴት ሰንሰለት ድርጊት መርሃ ግብር የሚጣጣም ብቁ የሆኑ ማንኛውም  አመልካቾች የፕሮጀክት ሃሳብ ሊያቀረቡ ይችላሉ፡፡  ሂደቱም፤-

**ለማህበረሰቡ ስለፕሮጀክት ንደፈ ሃሳባ አቀራረብ ግንዛቤ መፍጠና ጥሪ ማካሄድ፡** የእሴት ሰነሰለትን ለማሻሻል የቀረበ የመቀናጀ የፋየናንስ ምንጭ መኖሩን የገንዛቤ ፈጠራ መካሄድ ይኖርበታል፡፡ ዝርዝር የሆነ  የገንዛቤ መፍጠሪያ ድርጊት መርሃ-ግብር በወረዳ የቴክኒክ ኮሚቴና ባለድርሻ አካላት የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ የግንዛቤ ፈጠራው በሚመለከተው የወረዳ ጽ/ቤትና በአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ የሚከናወን ሲሆን በዓመት አንድ ጊዜ ወይም እንደሁኔታው በተደጋጋሚ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

አግሮ ቢግ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳቦችን ቤትኛውም ጊዜ (የጊዝ ገደብ ሳይኖረው) ይቀበላል፡፡ ለዚህም የሚያግዙ  ስለፕሮጀክት አቀራረብ ጥሪና ማሰተላለፊያ አጭር መመሪያና   ወጥ የሆነ የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳብ ማቅረቢያ ቅጽ (አባሪ 1) በበቂ ሁኔታ ተባዝቶ ለሥራ ዝግጁ ሆኖ መቀመጥ አለበት፡፡

የአግሮቢግ የወረዳ አሰተባባሪ ከወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በመሆን  ለመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ የፕሮጀክት ሃሳብ ጥሪን ያስተላልፋሉ፤ እንደመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ፡ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሰቦች እንዴት እንደሚጻፉ ያስረዳሉ፡፡ አስተባባሪው ማመለከቻዎችን ይቀበላል፡ እንዲጸድቁም ለቴክኒክ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

## 5.2 የቀረበን የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ መመርመርና ማጽደቅ

የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ ማመለከቻ ቅጽ አባሪ 1 ወጥ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን አመለካቾች ፍለጎታቸውን የሚገልጹበትና ለገምጋሚዎች የሚረዳ  መሰረታዊ መረጃዎችን የሚሰጥ ነው፡፡

አመልከቾች የፕሮጀከት ንድፈ-ሃሳባቸውን በቀጥታ ለወረደው አግሮቢግ አስተባባሪ መላክ አለበቸው፡፡ አስተባባሪውም የቀረቡለትን ማመልከቻዎች ሁሉ መዝገቦ በመያዝ ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ተሻሉትን ለመለየት ያቅባል፡፡ የቴክኒክ ኮሚቴ  አባለት ወይም  ኮሚቴወው በሚሰይመው ቡድን የተሸሉትን ንድፈ-ሃሳቦች ለዚህ  ተገባር በተዘጋጀው መገመገሚያ ወይም መለያ  ቅጽ (አባሪ 2)  በመጠቀም ይመረጣሉ፡፡   ለዚህም እንዲረዳቸው ከታች በተመለከቱት  የመልመያ መስፈርቶች መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

- **የእሴት ሰንሰለት (ጥያቄ ቁጥር 7) የፕሮጅከት ንድፈ-ሃሳብ** በተመረጠው የእሴት ሰንሰለት ጋር ያተኮረ መሆኑና በአመልካቹ የተለየውን የምርቱን ችግር ወይም እጠረት ከመቅረፍ አንፃር ያለው ፋይዳ

- **የንግድ ልማት እቅድ (ጥያቄ ቁጥር 8)** የፕሮጀክት ሃሳቡ እጥረቱን ለመቅረፍ ምን አደዳዲስ አሰራሮችን ይዟል፤ በፕሮጀክቱ ትግበራ አሁን ያለውን ችግር እንዴት እንደሚያስወግድ በመጨረሻ የሚገኘው መልክም ወጤት ምን እንደሆነ የሚያሳምን መሆን አለበት

- **የሚያመጣው አወንታዊ ተጽዕኖ (ጥያቄ ቁጥር 11)** ሊለካ የሚችል ውጤት ስለመኖሩ፤ ተጠቃሚው ማን እንደሆነ፤ የሚገኘው አወንታዊ ተፅዕኖ ዘላቂነትን ያለው መሆኑ፤ ሁሉንም ባለድረሻ አካላት ተጠቃሚ ከማድረግ አንጻር

- **የአመልካቹ የመፈፀም ብቃት (ጥያቄ ቁጥር 10)** የቴክኒክ ችሎታ፡ አስተዳዳራዊ ብቃቱ፤ የፋይናንስ አቅም፤ የያዛቸው ስራተኞች የሥራ ልምድና ብቃት በመጠቀም ፕሮጀክቱን በአጋባቡ ፈጽመው ግብን ከማሰካት አንፃር የሚመዘን ይሆናል፡፡

**ተወዳዳሪዎችን መምረጥ**

እያንዳንዱ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ በተመሳሳይ ጊዜ በሁለት ሙያተኞች ለየብቻ ነጥብ ይሰጣል፡፡ ከዚህ በታች በተመለከተው የመልመያ መስፈርት መሰረት ደረጃ የሰጣሉ፡፡

| መስፈርት | የተሰጠው ክብደት /ሀ/ | በገምጋሚው የተሰጠ ወጤት (ከ10) /ለ/ | ውጤት /ሐ = ሀ X ለ/ |
|---|---|---|---|
| ከእሴት ሰንሰለት አንፃር | 30% | 8 | 2.4 |
| የንግድ ልማት ዕቅድ | 30% | 8 | 2.4 |
| ከሚያስከትለው አወነታዊ ተፅዕኖ | 20% | 7 | 1.4 |
| የተወዳዳሪው ብቃት | 20% | 5 | 1.0 |
| **ድምር** | **100%** | | **7.2** |

ተወዳሪዎችን በመስፈርቱ አወዳድሮ ከመለይት በፊት የቴክኒክ ኮሚቴው  የመስክ ጉብኝት ሊያደረግ ይችላል፡፡ የጉብኝቱም ዓላማ ገምጋሚዎች አመልካቾችን ከዚህ በፊት የማያዉቋቸው ከሆነና በፕሮጀክት ንድፈ-ሃሳብ የቀረበው መረጃ ለማመሳከርና የመፈጸም ብቃታቸውን ለመፈተሽ ያገለግላል፡፡

### ብቁ ተወዳዳሪን ለይቶ ማጽደቅ

የእያንዳንዱ ገምጋሚ አማካኝ ውጤት በየፕሮጀክት ንደፈ-ሃሳቡ ከተሰጠ በኋላ የሁለቱ ገምጋሚዎች ነጥብ ተደምሮ አማካኝ ውጤት ይደረሳል፡፡ በውጤቱ መሰረት የወረዳው የቴክኒክ ከሚቴ  ለስትሪንግ ኮሚቴ  የምክረ ሃሰብ ያቀርባል፡፡ ስትሪንግ ኮሚቴው ከ7.0 ነጥብ በላይ ያገኙትን  ተስማምቶ ሊያጸድቀው ይችላል ካልሆነም ሌላ ውሳኔ ሊያሳርፍ ይችላል፡፡

## 5.3 ዝርዝር የፕሮጀክት ሃሰብ አዘገጃጀት

በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ላይ የሚውለው መዋለ ነዋይ የሚጠበቀውን ውጤት ለማግኘት የመጨረሻውን የፕሮጀክት ሃሰብ ተቀብሎ ለማስተናገድ እንዲቻል በተቻለ መጠን ጥሩ የፕሮጀክት ሃሳብ እንዲቀርበ ከፍተኛ እገዛ ይሻሉ፡፡

### ለአመልካቾች የፕሮጀክት ሃሳብ አፃፃፍ ስልጠና መስጠት

የፕሮጀክቱ ንድፈ-ሃሰብ ተቀባይነት እንዳገኘ አመልካቾች ስለዋናውና ዝርዝር ፕሮጀክት ሃሰብ አቀራረብ ከ1-2 ቀናት የሚቆይ ስልጠና ለመስጠት በአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ አማካኝነት ጥሪ ይተላለፋል፡፡ ሥለጠናው ከሚያካትታቸው ርዕሶች መካከል መሰረታዊ የእሴት ሰንሰለት ፈንድ ግቦች፤ የተፈቀዱና የተከለከሉ የወጪ ርዕሶች፤  ስለ ፕሮጀክት ሃሳብ አዘገጃጀት መመሪያ (የፕሮጀክቱ አወቃቀር፤ የፕሮጀክት አፈቃቀድ ሂደት፤ የውል ሰነድ፤ የክፍያ አጠያየቅና ግዢ፤ ሪፖርት፤ ክትትልና ምዘና፤ ኦዲት ስለማስደረግና አግበብነት በሌላቸው ተግባራት ምክንያት ሊከስቱ ስለሚችሉ ጉዳችን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ስልጠና ስለመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ የጋራ ግንዛቤ ይፈጥራል፡ ጥራት ያለው የፕሮጀክት ሃሳብ እንዲቀርብ እገዛ ያደርጋል፤ ትግበራውንም ያሳልጣል፡፡

### ለፕሮጀክት ሃሰብ ዝግጅት የሚደረግ ሙያዊ እገዛ

ከስልጠና  በኂላ አመልካቹ የፕሮጀክት ሃሰብና የስራ እቅድ ለማዘጋጀት በቁ አይደለሁም በሎ ካሰበ የወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ ሙያዊ እገዛ እንዲያደርግለት በስልጠና ወቅት ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ በስልጠና ወቅት ድጋፍ የሚሹቱን  መለየት ይጠበቅበታል፡፡

**ዝርዝር የመቀናጀ ድጋፍ የፕሮጀክት ሃሳብ ዝግጅት**

አመልካቾቾች በተዘጋጀው የፕሮጀክት ሃሰብ ማቅረበቢያ ቅጽ (**አባሪ 3**) **በ**መጠቀም ማዘጋጀተና ማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ የፕሮጀክት ሃሰቡን ለመፍቀድ እንዲቻል የሚከተሉትን ጉዳዮች ምላሽ መስጠት የኖርበታል፡፡ ብእሴት ሰንሰለት የተለዩ ችግሮችን ምላሽ የሚሰጥ  መሆን አለበት፤ ሊመዘንና ሊቆጠር የሚችል ውጤት የሚያመጣ መሆን አለበት፤ ውጤቱ በመጨረሻ ሲመዘን  በተጠቃሚዎች ዘንድ ተጨባጭ ለውጥ  የሚያሳይ መሆን አለበትና አባሪ 4 የተመለከቱትን ፊርጀ ብዙ ሁኔታወቸችን በአጋባቡ መመለስ ይጠበቅበታል፡ አመልካቾች የተሟላ  የፕሮጅክት ሃሳባቸውን ለአግሮቢግ አሰተባባሪ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን  አሰተባባሪውም መዝግቦ ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴው ያቀረባል፡፡

## 5.4 ማጽደቅና አመልካቹ ውል እንዲወስድ ማሰወቅ

የፕሮጀክት ሃሳቡ እንደደረሰ የቴክኒክ ኮሚቴው የተወሰኑ አባለቱን የፕሮጅከት ሃሰቡን እንዲመረምሩ ሊመድብ ይችላል፤ አስፈላጊ ከሆነም የውጭ አማካሪዎችን ሊጠቀም ይችላል፤ ለውጭ አማካሪዎች የሚፈፀም ክፍያም በጀት ይያዛል፡፡

**የብቃት ፍተሻ**

እያንዳንዱ የፕሮጀክት ሃሳብ በ3 ሙያተኞች በተናጠል በተመሳሳይ ጊዜ ወጥ በሆነ መስፈርት ይመዘናሉ፡፡ በጨረሻም የ3ቱ ውጤት በአማካኝ ተሰልቶ **በአባሪ 5** ቅጽ ተጠቃሎ ደረጃ ይሰጣቸዋል፡፡

**የማወዳደሪያ መስፈርቶች የሚከተሉት  የሆናሉ**

1) **የእሴት ሰንሰለት ፕሮጀክት ሃሳብ /ጥያቄ ቀጥር** 7ንድፈ-ሃሳብ በተመረጠው የእሴት ሰንሰለት ጋር ያተኮረ መሆኑና በአመልካቹ የተለየውን የምርቱን ችግር ወይም እጠረት ከመቅረፍ አንፃር ያለው ፋይዳ
2) **የንግድ ልማት እቅድ (ጥያቄ ቁጥር** 8)  እጥረቱን ለመቅረፍ ምን አደዳዲስ አሰራሮችን ይዟል፤ በፕሮጀክቱ ትግበራ አሁን ያለውን ችግር እንዴት እንደሚያስወግድ መጨረሻ የሚገኘው መልክም ወጤት ምን እንደሆነ የሚያሳምን
3) **የትግበራ ስልቱ /ጥያቄ ቁጥር** 9/  እቅዱን  ተመጣጣኝ በሆነ ገንዘበና ሊጨበጥ የሚችል ውጤት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ  ማሳካቱ
4) **የአመልካቹ የመፈፀም ብቃት (ጥያቄ ቁጥር** 10)  የቴክኒክ ችሎታ፡ አስተዳዳራዊ ብቃቱ፤ የፋይናንስ አቅም፤  የያዛቸው ስራተኞች የሥራ  ልምድና ብቃት በመጠቀም ፕሮጀክቱን በአጋባቡ  በመተግበራቸውና ግብን ከማሰካት አንፃር የሚመዘን ይሆናል፡፡

5) **ከሚጠበቁት ተጨማሪ ጥቅሞች አንፃር / ጥያቄ ቁጥር** 11/ ከፕሮጀክት የሚጠበቁ ጥቅሞች በውል ተለይቶ መገለጽ አለበት፡፡ ከትግበራው የሚገኘው ጥቅም ለፕሮጀክቱ ከወጣው ወጪ ጋር መነፃፀር ይኖርበታል፡፡

6) **ከታላሚ ተጠቃሚዎች አንጻር /ጥያቄ ቁጥር** 12/ የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው፤ በተለይ ሴቶችና ወደጎን የተተዉ ድሃ አርሶ አደሮች ወይም አንስተኛ ባለይዞታዎች ቅድሚያ ስለማገኘታቸው

7) **ከበጀት አንፃር /ጥያቄ ቁጥር** 13/ የቀረበው የማስፈጸሚያ በጀት ያልተጋነነና በመረጃ የተደገፈ የወጪ ግምት ሆኖ፤ በተለያዩ ርእሶች የተጠየቀው በጀት ከሥራው ጋር ከሚጠበቀው ውጤት አንፃር የተጣጣመ ስለመሆኑ

8) **ከመቀናጀ በጀት አንጻር /ጥያቄ ቁጥር** 14/ አመልካቹ የፕሮጀክቱን ምን ያህል ድርሻ በራሱ ገንዝበ (በጥሬ ገንዘብ) ለመሸፍን ይችላል ወይም ፍላጎተ አለው፡፡

9) **ሊሳኩ ከሚችሉ አመላካቾች አንፃር /ጥያቄ ቁፅር** 15/ የሚጠበቁ ውጤቶች ሊለኩ ሊደረስባቸው የሚችሉ ሆነው ወደ ትግበራ ሲገባ እንዴት የእሴት ሰነሰለትን እንደሚያዳብርና ተጠቃሚዎች እነማን እንደሆኑ የሚገኘው ውጤት ዘላቂነት ያለውና አንስተኛ በለይዞታዎችን የሚጠቅም ስለመሆኑ

10) ***ፈርጀ ብዙ ሁኔታዎች- ሥርዓተ-ፆታ*** /**ከመከታታያ ቅፅ** 1- 4/ ፕሮጀክቱ ሲታቀድ የሴቶችንና የወንዶችን ተሳትፎ በደንብ ግምት ውስጥ ያስገባና ሥርዓተ-ፆታን እንደዋነኛ ስራ በእቅዱ ውስጥ ያካተተ ስለመሆኑ

11) ***ፈርጀ ብዙ ሁኔታዎች- የአካባቢ እንክብካቤ*** / **ከመከታታያ ቅፅ** 5-8/ የፕሮጀክተ ሃሳቡ ሲቀርብ የአካባቢ ደኅንነት በደንብ ግመት ውስጥ ገብቶ ተዘጋጅ መሆን አለበት፡፡ አስፈላጊ ከሆነና ተፅዕኖ የሚያስከትል ከሆነ ችግሩን ለመቀነስ ያሰቀመጠው መፍትሄ በፕሮጀክት ሃሰቡ መታየት አለበት፡፡

### ***የመስክ ግምገማ***

*አስፈላጊ ሲሆን የገምጋሚው ቡድን በፕሮጀክት ሃሳቡ የተካተቱ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የመስክ ምልከታ ሊያካሂድ ይችላል፡፡ ለዚህም የፕሮጀክት ታላሚዎችን ወይም አመልካቾችን ቃለ-መጠይቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ሥርዓተ-ፆታን በዝርዝር መመልከት ይቻላል፡፡*

### ***ፈርጀ ብዙ ጉዳደችን መገምገም***

*ገምጋሚው ቡድን የሥርዓተ-ፆታና የአካባቢ ደህንነት ጉዳይ በፕሮጀክት ሃሰቡና በእቅድ ዝግጅት ወቅት በበቂ ሁኔታ መካተቱን መረጋገጥ አለበት፡፡ አሰፈላጊ ከሆነም ተጨማሪ መወሰድ ያለባቸዉን እርመጃዎች መከለስም ካለበት በውሳኔ ሃሰቡ መካተት ይኖርበታል፡፡*

*ማደማደሚያና ምክረ ሃሳቦች*

በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ የፋይናንስ ምንጭ የሚከናወን እንቨስትመንት በተቻለ መጠን በርካታ ቁጥር ላለው አርሶ አደር ጥቅም ስለማስገኘቱና ፕሮጀክቱም የፋይናንሰ አዋጭነቱ መረጋገጥ አለበት፡፡ የገምጋሚው ቡድን የፕሮጀክት ሃሳቡን በቴክኒክ ብቃቱና በሌሎች መመልመያ መስፈርት መመዘን ያለበት ሲሆን አስፈላጊ ከሆነም የሚሰጠው አስተያት የትግበራውን ስልት ወይም በጀቱን እስከመቀይር ድረስ ሊሆን ይገባል፡፡

በመጨረሻም ገምጋሚው ቡድን የጠረጼዛና የመስክ ግመገማውን ካካሄደ በኋላ ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ማደማደሚያና ምክረ ሃሳቦች ያቀርባል፡፡

- **አጠቃላይ ማደማደሚያ** ፡- በቀረበው የፕሮጀክት ሃሰብ ላይ በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊና በቴክኒክ ዙሪያ ያለውን ድርሻ ግልፅና አጥር ያለ አስተያየት ማስፈር

- **ምክረ ሃሳብ** ፡- የቀረበው ፕሮጀክት ሃሰብ የበቴክኒከ ኮሚቴው እንዲያጸድቀው ወደም ወደ አመለካቹ ተመልሶ ተከልሶ እንዲቀረብ ወይም ብቁ ባለመሆኑ ውድቅ መሆን እንዳለበት እንደሚያመላክት ይጠበቃል፡፡

**በአብቁተ የሚደረግ የፕሮጀክት ሃሳብ ግምገማ**

የአብቁተ ቅ/ጽ/ቤት ተወካይ በወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ ይሳተፋል፤ በሚቅረበው የሥራ እቅድ ላይ ሙያዊ ምክር ይሰጣል፡፡ የሚቀረበው የፕሮጅክት ሃሰብ ለብድር ብቁ ከመሆን አንጻር እገዛ ያደርጋል፤ አብቁተ ከመጀመሪያው ጀምሮ በፕሮጅከቱ ላይ ማሰተፉ ከዘላቂነት አንፃር ከፍተኛ አሰተዋጽዖ ይኖረዋል፡፡

**በወረዳ ስትሪንግ ኮሚቴ ማጽደቅ**

የእያንዳንዱ ገምጋሚ አማካኝ ውጤት በየፕሮጀክት ንደፈ-ሃሳቡ ከተሰጠ በኋላ የገምጋሚዎች ነጥብ ተደምሮ አማካኝ ውጤት ይደረሳል፡፡ በተገኘው ነጥብ መሠረት ለእያነዳነዱ የፕሮጀክት ሃሰብ የማጠቃለያ ደረጃ ይሰጣል፡፡ በተገኘው ውጤትና ደረጃ እንዲሁም በአብቁተ ግምገማ መሠረት የወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ አመልካቹ በራሱ ማወጣት ያለበትን የመቀናጀ በጀት (15%) ጨምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለስሪንግ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

የወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ የቀረበለትን የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ምክረ ሃሳብ ከተመለከተ በኂላ ስትራቴጂካዊና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመለየት፤ ከፕሮጀክት ቦታ ወይም ከአካባቢ ምርጫ አንፃር፤ ከሚጠበቁ ውጤቶችና ከፋይናንስ አቅም ጋር አገናዝቦ የመጨረሻ ውሳኔ ያስርፋል፡፡

**የአግሮ ቢግ ስምምነትና የፕሮጀክት መፈቀድን ሰለማሳወቅ**

የወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ ውስኔ ለአግሮቢግ ፕሮገራም ድጋፍ ዩኒት ፈንድ ጽ/ቤት የመጨረሻ ግምገማ ይልካል፤ አግሮቢግም ስምምነቱን ለውረዳዉ እንደገለጸ የፕሮገራሙ ወረዳ አሰተባባሪ የተመረጠውን አመልካች ያሳውቃል ያልተመረጡ ተወዳዳሪዎችም ሂደቱንና ውጤቱን እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

## 6. የድግፍ ፕሮጀክት ትግበራ

### 6.1 ሕጋዊ የውል ስምምነት

የፕሮጀክት ሃሳቡ ተቀባይነት እንዳገኘ ወደትግበራ ይገባል። ወደትግበራ ለመግባት ፕሮጀክቱ ስለሚተገበርበት ሁኔታ በተመረጠው አመልካችና በፈንዱ ስክሪታሪያት መካከል ሕጋዊ የውል ስምምነት ይፈረማል። በሁሉም ፕሮጀክቶች ወጥ የሆነ የውል ስምምነት ቅጽ (አባሪ 6) እንዲኖር ታስቦ ናሙናው ከዚህ ማኑዋል ጋር አበሪ ሆኖ ተያይዟል።

የፈንዱ ሴክሪታሪያት ጽ/ቤት ፕሮጀክቱን ለመተግበር እንደተመረጠው አመልካች አቅም ሁኔታጋር ታይቶ ከትግበራ በፊት ስልጠና ሊያዘጋጅ ይችላል። የስልጠናው ርዕስም በክፍያ አፈፃፀምን የግዢ ሥርዓት፤ በፋይናንስ አስተዳደርና ሂሳብ አያያዝ፤ በሪፖርት አዘገጃጀት፤ በኦዲትና በፕሮጀክት ክትትለና ምዘና ይሆናል ዙሪያ ይሆናል።

### 6.2 የባንክ ሂሳብ ቁጥርና የክፍያ አፈፃፀም

ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገው ቅድሚያ ክፍያ ከመለቀቁ በፊተ ተጠቀሚው ድርጅት ቅድሚያ በአበቁተ በፕሮጀክቱ ስም ልዩ የባንክ ሂሳብ ቁጥር መክፈት ይጠበቅበታል። ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ክፍያ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ብቻ የሚንቀሳቀስ ይሆናል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሂሳብ ቁጥሩ ለብቻው የሂሳብ መዝገብ ከሌላ ጋር ሳይቀላቀል ይቋቋማል።

#### የገንዘብ ፍላጎት ሰንጠረዥና ክፍያ አጠያየቅ

የተመረጠው ድርጅት በትግበራ ወቅት በተለያየ ጊዜ የሚስፈልጋቸውን የገንዘበ ፍላጎት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከፕሮጀክት ሃሳቡ ጋር ተካቶ መቅረብ ይኖርበታል። ተከታታይ ክፍያዎችን ተጠቃሚው በጽሁፍ ጥያቄውን ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን ከዚሁ ጋር ወቅታዊ የአፈጻጸም ሪፖርትና ለክፍያው አስረጅ የሆኑ ደጋፊ ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ አለበት።

#### የመጨረሻ ክፍያ

የፕሮጀክቱ የመጨረሻ ክፍያ (የፕሮጀክቱ ጠቅላላ ወጪ 5%) የሚለቀቀው ስለፕሮጀክቱ አፈፃፀም የማጠናቀቂያ ሪፖርት ተዘጋጅቶና ለፈንዱ ሴክሪታሪያት ቀርቦ፤ ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዘ ማንኛውም የተጠለጠሉ ጉዳዮች ሁሉ እልባት አግኝተውና የፕሮጀክቱ ፋይል ከተዘጋ በኋላ ይሆናል።

### 6.3 ግዢ

የፕሮጀክቱ ተግባሪ ድርጅት ከተፈቀደው ፕሮጀክት ላይ ግዢ ሊያከናውን ይችላል። ግዢ በሚፈጸምበት ወቅት ሥራ ላይ የሚውለው የክልሉ መንግስት በሚከተለው የግዢ ሥርዓት ይሆናል። የፈንዱ

ሴክሪታሪያት ጽ/ቤት ፈፃሚዎች የሚመሩበት የግዢ ማኑዋል ያዘጋጃል ለትገበራም እንዲያግዝ ለሚመለከታቸው ሙያተኞች ስልጠና ይሰጣል፡፡

**ከገዢ በፊት የአግሮቢግን ስምምነት ማግኘት፡** የፕሮጀክት አስፈጻሚው የግል ተቋም ከሆነ የግዢ ውል ከመያዙና ግዢ ከመፈጸሙ በፊት ስለተከተለው የግዢ ሥርዓት ከመንግስት የግዢ ሥርዓት አንፃር መታየት ስላለበት ከፈነዱ ሴክሪታሪያት ወይም የወረዳውን አግሮቢግ ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡

## 6.4 የፋይናንስ አስተዳድርና የሂሳብ አያያዝ

የፈንዱ ተጠቃሚ ድርጅት ተገቢና ግልጽ የሆነ የፈንድ አስተዳደር የመዘርጋት ሃላፊነት አለበት፡፡ በአተገባበር ላይ ብክነት ወየም ያልተፈቀደ ክፍያ ተፈፅሞ ቢገኝ ለፕሮጀክቱ የሚለቀቀው ገንዘብ እንዲቋረጥ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ አግባብነት የሌለው ወጪ ተፈፅሞ ቢገኝ ለፕሮጅክቱ ገንዘቡ ተተክቶ ወጪው በፈፃሚው ድርጀት የሚሸፍን ይሆናል፡፡

### የሂሳብ አያያዝ

ለእያንዳንዱፕሮጀክት ከሌላ ሂሳብ ጋር ሳይቀለቀል ለብቻው ተገቢ የሆነ የገቢና ወጪ መዝገብ ይቋቋማል፡፡ ተፈላጊ መረጃዎች በሙሉ በሂሳብ መዝገቡ መሞላት ያለባቸው ሲሆን ለምዝገባ መነሻ የሆኑ የሂሳብ ሰነዶች (የግዢ ማዘዣዎች፤ ደረሰኞች፤ አቅራቢዎች የተለዩበት ማብራሪያ…) ለአስረጅነት መያያዝ አለባቸው፡፡

የፕሮጀክት ተገባሪው ድርጅት አሰቀድሞ በተፈረመው ውል መሰረት የሂሳብ መግላጫ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዘ ማንኛውም መዝገብ፤ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርቶች፤ ደጋፊ የሂሳብ ሰነዶች፤ ወዘተ… ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀና አግሮቢግ ሂሳቡን አስመርምሮ የኦዲት ሪፖርት ከወጣ በኋላ ቢያንስ ለ3ዓመታት በአግባቡ ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

## 6.5 የሩብ ዓመት ክንውን ሪፖርት

የፈንዱ ተጠቃሚ ድርጅት **በአባሪ 7** ቅጽ መሰረት የየሩብ ዓመት የተሟላ የአፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡ ሪፖርቱ ለወረዳው አሰተባባሪ የሚሰጥ ሆኖ አስተባባሪው የሁሉንም አዘጋጅቶ ለውረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ ኮሚቴውም የራሱን አስተያየት አካቶ ለወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ ይለካል፡፡

## 6.6 የፋይናንስ ሪፖርት

በተመሳሳይ በየሩብ ዓመቱ የመጨረሻ ወር ላይ የፕሮጀክቱን የገቢና የወጪ ሪፖርት አዘጋጅቶ መላክ ይጠበቅበታል፡፡ የፕሮጀክቱ ለቀጣይ ሩብ ዓመት የሚያስፈልገው ገንዘብ የሚለቀቀው ያለፈው

ሩብ ዓመት የፋይናንስ ሪፖርት ሲቀርብ ብቻ ይሆናል፡፡ የፋይናንስ ሪፖርቱ ከሥራ ክንውን አፈፃፀም ሪፖርት ጋር ተያይዞ መላክ አለበት፡፡

የየሩብ ዓመቱ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ አባሪ 8 ከዚህ ማኑዋል ጋር የተያያዘ ሲሆን የፕሮጀክቱየተፈቀደው በጀት በየንኡስ አርእስቱና የወጪ ሂሳብ መደብ ይሞላል፡፡ የባለፉት ሩብ ዓመታትና የወቅቱ ሩብ ዓመት ወጪ በተዘጋጀላቸው ቦታ የሞላል፡፡ ከተፈቀደው ጠቅል በጀት እስካሁን የወጠጣውን የወጪ ድምር በመቀነስ ድርጅቱ ያለተጠቀመበትን ወይም ሥራ ላይ ያልዋለውን በጀት ያገኛል፡፡

## 6.7 ክትትልና ቁጥጥር

የወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴና የወረዳው ፕሮገራም አስተባባሪ ፕሮጀክቶች እንዴት እየተከናወኑ እንደሆነ ወደመስክ እየተወጣ ተከታታይ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### በመከናወን ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን ክትትል ማድረግ

የወረዳው ፕሮገራም አሰተባባሪ በመከናወን ላይ ያሉ የሁሉንም ፕሮጀክቶች ሪፖርት በመረከብ ምዝገባ በማከሄድ አፈፃፀሙን ከዕቅዱ ጋር ያነፃጽራል፡፡ በመቀጠልም

1. የፋይናንስ ሪፖርት በትክክል መዘጋጀቱንና አስፈላጊ ደጋፊ ሰነዶች መያያዛቸውን ያረጋግጣል
2. ከፈንዱ ተጠቃሚ በደረሰው የቅድሚያ ክፍያ ጥያቄ መሰረት በቀጣይ 3 ወራት የሚያስፈልገውን ገንዝብ በማዘጋጀት ለሴክረታሪያት ጽ/ቤት ይልካል
3. አጠቃላይ የፕሮጀከትን አፈፃፀም በተለይ ከእቅዱ አንፃር የሚያሳይ አጠር ያለ የማጠቃለያ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

የወረዳው ፕሮገራም አስተባባሪው በትግበራ ላይ አፋጣኝ ምላሽ የሚሹትን ችግሮችን ተሎ ምላሽ መስጠት ያለበት ሲሆን ችግሮችን መከነመፍትሄ ሃሰቦቻቸው ጋር ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴው ያሳውቃል፡፡

### የመስክ ቁጥጥር

የወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴው ሀሉንም ፕሮጀከቶች መስክ በመውጣት የሚጎበኝበትን ጊዜ አስቀድሞ እቅድ ያወጣል፡፡ የመስክ ጉብኝት የሚደረገው ቡድን አባላት የወረዳው ፕሮገራም አስተባባሪ እና ከቴክኒክ ኮሚቴው አባለት መካክል ወይም አገልገሎት ከሚሰጡ የውጭ አካላት በመመደብ ይሆናል፡፡ የመስክ ጉብኝቱ ሳይቆራረጥ ማከናወን ያስሰፈለገበት ዋናው ምክንያት

- የፋይናንሰ አሰተዳደሩና አደረጃጀቱ ትክክል መሆኑንና ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ በትክል ሪፖርት መደረጉን ለማረጋገጥ

- የተከናወነው ተግባር በእቅድ ከተያዘው አንፃር ምን ያህል እነደሆነ ለማጣራትና ለሚቀጥለው ሩብ ዓመት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለመልቀቅ የሚስችል ሁኔታ እንዳለ ለመፈተሽ ነው፡፡

በትግበራዉ የመጀመሪያ ጊዜ ግትትል ማድረግ ሥራ ላይ የዋለው ገንዝብ በስምምነቱ ለተጠቀሱ ተግባራት ላይ መዋሉንና ግዢዎች ስርዓቱን ጠበቀው የተከናወኑ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ይጠቅማል፡፡

### የፕሮገራሙን የፋይናንስ አስተዳደር ማኑዋል ባለመተግበር ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮች

የፈንዱ ተጠቀሚ ድርጅቶች ይህን ማኑዋል ባለማከበራቸው በመጀመሪያ የሚወሰድው እርምጃ የሚቀጥለውን ሩብ ዓመት የሚለቀቅ ገንዝብ ሊያሰርዝ ችላል፡፡ ቀጥሎም በጉዳዩ ላይ በቂ ማብራሪያ ካልተገኘ ልዩ የሂሳብ ኦዲት እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ አሁንም ከፕሮጀክት ተጠቃሚው ወገን በቂ ትብብር ካልተገኘ ተጨማሪ ጉዳት ከማስከተሉ በፊት ወዲያዉኑ ፕሮጀከቱ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደት ወንጀል የተፈጸመ ከሆነ፤ ወይም የፕሮጀክቱ ገንዘብ ባክኖ ከተገኘ ገነዘቡ እንዲተካና በአጥፊዎችም ላይ በፈፀሙት እምንት ማጉደል የፈንዱ ሴክረታሪያት ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡

## 6.8 የማጠናቀቂያ ሪፖርትና ፕሮጅክትን መዝጋት

ፕሮክትን በአግባቡ ማጠናቀቅንና ሥርዓቱን ጠብቆ መዘጋት አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ድርጅት ሲያካነውን የቆውን ፕሮጀክት ከመዝጋቱ በፊት ያልተጠናቀቁ ምዝገባዎች፤ በሚመለከተው አካል ያልፀደቁ በፕሮጀክቱ የተገኙ የስራ ውጤቶችና ያልተጠናቀቅ የፋይናንስ ጉዳዮች በሙሉ በተገቢው መልኩ መጠናቀቅ አለባቸው፡፡

እንዲሁም ባልተጠናቀቁም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ከፕሮጀክት ፈጻሚው ጋር መልካም የስራ ትብብር እንዲኖር ለማስቻል የመጨረሻ የፕሮጀክቱ 5% ክፍያ የማጠናቀቂያ ሪፖርት ከተዘጋጀና ከቀረበ በኂላ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

### የማጠናቀቂያ ሪፖርት

ፕሮጀክቱን ሲከናውን የቆየው ድርጅት ለዚህ ሲባል በተዘጋጀውየፕሮጀክት ማጠናቀቂያ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ በአባሪ 10 መሠረት አዘጋጅቶ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ የሪፖርቱ ይዘቱም ያለፉትን ሩብ ዓመታዊ ሪፖርቶችን አጠር አድረጎ አጠቃሎ ያያዘ፤ በፕሮጀክቱ የውል ስምምነት በተጠቀሱ ዋና አማላካቾች መሠረት የተገኙ ውጤቶች የዳሰሰ መሆን ይኖርበታል፡፡

### ፕሮጀክቱን መዝጋት

በወረዳ ደረጃ ፕሮጀክቶችን ለመዘጋት የሚያስፈለገውን መድረክ የማዘገጀት ሃላፊነት የወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴና የውረዳ አግሮቢግ አስተባባሪ ድረሻ ነው፡፡ ፕሮጀክቱን ለመዝጋት ከሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች መካከል

1. አንድ ወይም በርካታ የሆኑ ከተወሰኑ ባለድርሻ አካላት ጋር ተኮር ውይይት ማከሄድ /አባሪ 11/ በመጠቀም
2. ከፕሮጀከቱ ውጤት ተጠቃሚዎች ያገኙትን ጥቅም በምስክርነት ማሰባሰብ /አባሪ 12/
3. ሁሉም ያለተከፍሉ የተጠለጠሉ ሂሳቦች መከፈላቸውን፤ ሥራ ላይ ያለዋለ ገንዘብ መመለሱን በማረጋገጥ ሂሳብን መዘጋት
4. ከፕሮጀክት አሰፈጻሚው የቀረበውን የማጠናቀቂያ ሪፖርት ማጽደቅ
5. ኦዲት በማስደረግ ግድፈት የሌለበት የኦዲት አስተያየት ሪፖርት መቀበል
6. የፈንዱ ሰክረታሪያት ለፕሮጀት ፈጻሚው አካል ፕሮጀክቱ ስለመዘጋቱና ሁሉም ተፋላጊ ነገሮች መሟላተቸውን የሚገልጽ ደበዳቤ መፃፍ፤ ከዚህ በኋላ የሂሳብ ሰነዶች ለመንግስት ኦዲት ቢያነስ ለ3 ዓመት መጠበቅ እንዳለባቸው ማሳወቅ
7. ቀሪውን የመጨረሻ የፕሮጀክቱን 5% ክፍያ እንዲፈፀም ማደረግ ይሆናል፡፡

## 7. የማጠናቀቂያ ሂሳብ ምርመራ (ኦዲት)

የተሰጠው የፕሮጀክት ድጋፍ ፈንድ የህዝብ ሀብት እንደመሆኑ መጠን አስቀድሞ በተደረሰው ስምምነት መሠረት ገንዘቡ በአገባቡ ሥራ ላይ ስለመዋሉና የሂሳብ አያያዙ ትክክል መሁኑን ለማረጋገጥ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡

የፈንዱ ሰክረታሪያት ጽ/ቤትና የወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ እንደተጠናቀቀ ወዲያወኑ በመንግሰት ወይም አገልገሎቱን በሚሰጡ የውጭ ኦዲተሮች እንዲመረመር ያደርጋሉ፡፡

በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ትግበራ የተዘጋን ፕሮጀከት ኦዲት ማስደረግ ከሚከናወኑት ሥራዎች አንዱ ነው፡፡ ሂሳቡን ለማሰመርመር የሚስፈለገውን የአገለግሎት ክፍያ የሚውል በአግሮቢግ የፕሮገራም በጀት ተበሎ ተይዟል፡፡ ምርመራው በፋይናንስ ጉዳዮች የጠራ መረጃ ከመስጠቱም ባሻገር በፕሮጀክቱ ከተቀመጡት ዋና ዋና አመላካቾች አንፃርም የተገኘው ውቴትም የሚረጋገጥበት ዘዴ ነው፡፡

ማንኛውም የፕሮጀክቱ የፋይናንስና የግዢ ሰነዶች ፕሮጀክቱ ተዘግቶና ኦዲት ተደርጎ የኦዲት ሪፖረቱ ከወጣ ቢያንስ ለ3ዓመት በመነግስት አካል ለሚደረግ እንሰፔክሽን/ኦዲት ክፍት ሆኖ መጠበቅ የኖርበታል፡፡

## 8. የፕሮጀክት ውጤትን መመዘንና የመጣውን አወንታዊ ተፅዕኖ መዳሰስ

**ውጤት፡** ከፕሮጀከቱ በእሴት ሰንሰለት ላይ ተከስተው ለነበሩ እጥረቶች ተጨባጭ መሰረታዊ ለውጦች ወይም መፍተሄ የሚጠበቅ ሲሆን እነሱም አዲስና የተሞከረ የአሰራር ዘዴ መምጣቱ፤ የተሞከረ የድህረ-ምርት አያያዝና ብክነትን የቀነሰ ስልት ሰለመገኘቱ፤ የተሻሻለ የማቀነባበርና የአሰተሻሸግ ዘዴን ያመጣ ሥለመሆኑ፤ ገበያን የሚያበረታታና የሚያስፋፋ ሃሳብና የመሳሰሉት ከሚጠበቁ አይነተኛ ለውጦች ናቸው፡፡

በዚህ ፕሮጀክት የተገኙ ለውጦች አግሮቢግ በሌሎች ከፍሎች አሳካቸወለሁ በሎ ከያዘቸው ተግባራት ጋር መተሳሰር ያለባቸው ሲሆን ለምሳሌ አንሰተኛና ከንግድ ጋር የተሳሰረ የግብርና እንሸስትመንት

ማሰፋፋትና ይህም ቀጣይነቱን ይዞ መዝለቁን በዚህም  በረጅም ጊዜ አንስተኛ ባለይዞታዎች ዘንድ ድህነትን መቀነስ ከሚለው ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡፡

**ከፕሮጀክቱ የሚጠበቀው የረጅም ጊዜ አወነታዊ ተፅዕኖ** የሚረጋገጠው በግብርና ላይ የተሰማሩ አንስተኛ ባለይዞታዎች በመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ ፕሮጀክት በመሳተፍ የግብርና ምርትን ከገበያ ጋር በማተሳሰር በድህነት ቅነሳ የታየው ለውጥ ነው፡፡ በረጅም ጊዜ የሚታዩ አወነታዊ ተፅዕኖዎች የሚረጋገጡት የገበሬዎች ምረታማት በከፍተኛ ደረጃ በማደጉ ገቢያቸው በከፊትኛ ደረጃ ሲሻሻል፤ ምረታቸውን በተሻለ የመሻጫ ዋጋ ሲሸጡና በእሴት ሰንሰለት ተግባር ላይ የተሰማሩ ደርጅቶች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ነው፡፡ የሴቶች ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ ይሻሻላል ተብሎ ይጠበቃል፡፡  በአብዛኛወ የረጅም ጊዜ በፕሮጀክት ትግበራ ምክንያት  የመጡ መሰረታዊ  ለውጦችና እድገት የሚከሰቱትን ሊለኩ የሚችሉት  ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው፡፡

**የረጅም ጊዜ ለውጥን ለመፈተሽ የሚረዱ አመላካቾች**፡ በመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ  የመጣ መሰረታዊ ለውጦች በእያንዳንዱ ፕሮጀክት በተናጠል ወዲያዉኑና በመካከለኛ ጊዜ በተገኙ ውጤቶች ይለካል፡፡

**የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ ውጤት ከክትትልና ምዘና አንፃር የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ**




## የመቀናጆ ድጋፍ ፈነድን  ወጤት /Result/ መለካት

የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድን  ሂደት አሃዛዊ መለኪያዎች በቴክኒክ ኮመቴው የሚሰበሰብ ሲሆን የአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪው እገዛ ያደርጋል፡፡ መረጃው በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት ይደረጋል፡፡ የሚሰበሰበው መረጃ

1. የቀረበ የፕሮጅክት ንድፈ ሃሳብና የፕሮጀክት ሃሳብ ቁጥር
2. አማካኝ ክበደት ዋጋ የተሰጠው የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ (ከተገመገመው ፕሮጀክት ሃሰብ ቁጠር ጋር)
3. አማካኝ ክበደት ዋጋ የተሰጠው የፕሮጀክት ሃሳብ (ከተገመገመው ፕሮጀክት ሃሰብ ቁጠር ጋር)
4. የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ ማመልከቻዎች ተቀባይነትና ሊለካ ከሚችል አመላካች ውጤታማ አፈፃፃም ያሳዩ ፕሮጀክቶች መቶኛ ድርሻ (ከፕሮጅከት ሃሳብ ጥያቄ ቁጥር-15)

5. በየሩብ ዓመቱ በተፈቀደ የድጋፍ ፈንድ ተከፈለ የገንዘብ መጠን ከሩብ ዓመቱና ካለፉት ሩብ ዓመታት መቶኛ ድርሻ

6. የተፈቀድ የፐሮጀክት ሃሳበ እና በከፍተኛ ደረጃ ፈጠራ የታየበት ፕሮጀክት ቁጥርና መቶኛ ድርሻ (የፕሮጀከት ሃሰብ መገምገሚያ መስፍረት ጥያቄ ቁጥር- 7 ለ)

7. በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ በተሰጠ ድጋፍ የተሳተፉ የሴቶች መቶኛ ድርሻ

8. በተፈቀደው ድጋፍ ልዩ መፍትሄ ይዘው የመጡ ፕሮጀክቶች ቁጥር (ከፕሮጀከት ሃሳብ ጥያቄ ቁትር- 7)

## 2. በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ የተገኘን ውጤት ጥራት መዳሰስ (አሃዘዊ ባልሆኑ መለኪያዎች)

**Qualitative Assessement of VCF results** (መረጃው በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ሊጠናቀር ይችላል፡፡

1. **ቡድን ተኮር ወይይት ማከሄድ /አባሪ 11/** አባላት በፕሮጀክት ሃሳባቸው ያስቀመጡትን ዓላማ ማሳታቸውን በጋራ እንዲወያዩ እድል በመስጠት ሲሆን ምናልባት አላማቸውን ካላሳኩ ለዚህ ችግር ምን ምክንያቶች እንደነበሩ በጋራ የሚፈትሹት ይሆናል፡፡ ከዚህም ባሻገር ከሂደቱ ምን ተሞክሮ እንዳገኙ፤ በሌላ በተለየ መልኩ እንዴት ቢሰራ ኖሮ የተሸላ ውጤት ይገኝ ነበር በሚለው ወይይት ይደረጋል፡፡ ቡድኑ ከሂደቱ ለአባላት ምን ጥቅም እንዳስገኘ በተለይም የተሻለ ምርት ከማምረት አንፃር፤ ጥሩ የመሻጫ ዋጋ በማግኘት ረገድ፤ ኪሳራን በመቀነስ በኩል ወይም የተገኘ ተጨባጭ ጥቅም አንፃር ዳሰሳ ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ ቡድኑ የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ በመጠቀም ምክንያት በመሰረታዊነት ምን የተለየ ውጤት እንደተገኘ ፍተሻ ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በአግሮቢግ ክትትልና ምዘና አባላት በሚያጠናቅሩተ ሪፖርት የሚካተት ይሆናል፡፡

2. **የተጠቃሚዎችን ምስክርነት ማሰባሰብ /አባሪ 12/** ከተወሰኑ የቡድን አባለት ጋር ሰለሳለፉት ልምዳቸው የጠለቀ ውይይት ማካሄድ ሲሆን በተቻለ መጠን አባላት ሲመረጡ ሁሉንም አባላት ሊወክሉ ስለመቻላቸው እርግጠኛ መሆን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ውይይት ላይ አባላት በግለሰብ ደረጃ ያገኙትን የተጠቀሙትን ፊት ለፊት ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡ ተሳታፊዎች ለማመስገን ሳይሆን በትክክል የተገነዘቡትን አሰተያየታቸውን እንዲሰጡ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ውይይቶች (ታሪኮች) ከመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ የተገኙ የተማርናቸው ተሞክሮዎች ተብለው በአግሮቢግ ክትትልና ምዘና ቡድን ሪፖርት የሚካተት ይሆናል፡፡

በሁለቱም ዘዴ የተገኙ የተጠቃሚ መረጃዎች የፕሮጀክቱን ውጤት ለመተንትን እንደግብዓት ሁኖ ከማገልገሉም በላይ በፕሮጀክቱ ማጠቃለያ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

## 3. አሃዛዊ የእሴት ሰንሰለት መረጃ

ይህ መረጃ ከሂሳብ ምርመራ ሪፖርት ማግኘት የሚቻል ሲሆን ከሚፈለጉት መረጃዎች መካከል

9. የየድርጅቶች የሽያጭ ምልልስ

10 የሽያጭ ምልልስ ከተለያዩ እሴት ሰንሰለት አንፃር

11. ለእያንዳንዱ አባላት ከእሴት ሰንሰለት የተከፈለ የገንዘብ መጠን

12. የግብዓት ሽያጭ

13. በየማህበራት ያለው የአባለት ብዛት /ሴት ወንድ ድምር/

14. በየማህበራት ያለው ቋሚ ሰራተኛ ብዛት /ሴት ወንድ ድምር/

4. አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የአግሮ ቢግ ከትትልና ምዘና ቡድን በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ተገኝን **የአባላት እርካታ ዳሰሳ ጥናትና ሌሎች ጥናቶችን** ተጨማሪ መረጃዎች ሲፈልግ ሊደርግ ይችላል፡፡ የተጠቃሚዎች እርካታ፤ እምነት፤ የፋይናንስ አቅርቦት በቀላሉ መገኘት የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድን ውጤትማነተ አማላካቾች ናቸው፡፡

15) በእሴት ሰንሰለት የሚሳተፉ አካላት በቀላሉ የበግበዓት፤ የኤክሰቴሽን፤ የንግድ፤ የእንቨስትመንት፤ የፋይናንስ አቅርቦት፤ የማቀነበባበር እደሎችን በመጠቀም ያላቸው እርካታን እምነት

16) እነዚህ አካላት በትርፋማነት፤ በገበያ ላይ ያለ ፍላጎትና የተረጋጋ ገበያ በመኖሩ ምክንያት ያገኙት እምነትና እርካታ

አግሮቢግ ሁሉንም የተሳተፈባቸው ተጋበራትና የተገኙ ውጤቶች ላይ በየዓመቱ ትንትና ያዘጋጃል፡፡ ለምሰሌ በመቀናጀ ድጋፍ የተገኙ ውጤቶች ከገአግሮቢግ አስተዋጽዖ አንጻር ይጠናል፡፡ ይህም በፕሮገራሙ አመታዊ የክትትልና ምዘና ሪፖርት የሚካተት ይሆናል፡፡ የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ትግበራ ከአጠቃላይ የአግሮቢግ ከሚጠበቅ ውጤት ጋር ይመዘናል፡፡

**የፕሮገራሙ ወጤት አማላካች**

17) በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ዘላቂነትና እደገት ያለው እንቨስትመነት ግብርና ነክ የተሰጠ ድግፍ በቁፕርና በመቶኛ

AgroBIG

## አባሪ 1፡ የፕሮጀክት ንድፈ-ሃሰብ ማቅረቢያ ቅፅ

**የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ**

(እባክዎትን ሁሉንም ጥያቄዎች ይመልሱ)

1. **የአመልካቹ ስምና አድራሻ**

2. **ስለ አመልካቹ አጭር መግለጫ፡** ሀ) ህጋዊ ሰውነት፤ ለ) የተሰማራበት የሥራ መስክ፤ ሐ) ባለፉት 3 ዓመታት ያንቀሳቀሰው የሃብት መጠን ፤ መ) የያዘው የሰራተኛ ብዛት

3. **ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው** ሀ) ስም ለ) በመ/ቤቱ ያለው ሃላፊነት ሐ) አድራሻ መ) ስልክ ቁጥር ሠ) ኢሚል

4. **የፕሮጀክቱ መጠሪያ ስም**

5. **ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ (ወረዳ ቀበሌ)**

6. **ፕሮጀክቱ የሚተገበርበት ጊዜ**

7. **የእሴት ሰንሰለት የፕሮጀክት ሃሳብ** የተለዩትን ችግሮች ወይም እጥረቶች ምላሽ በመስጠት ምን ያህል አግባብነት አለው

8. **የንግድ ልማት ዕቅድ** የሥራ ዕቅዱ እንዴት የሚታሰበውን ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል የሚያሳይ መሆን አለበት።

9. **የሚከናወኑ ተግባራት፡** ፕሮጀክቱን ለመተግበር የሚከናወኑ ሥራዎች

10. **ፕሮጀክቱን ለመተግበር ድርጅቱ ያለው ብቃት፡** ሀ) ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ሥራ ያለው ልምድ፤ለ) ወደ ሥራ የሚያሰማራቸው ሰራቶኞች የትምህርት ዝግጅት ሐ) የፕሮጀክት ፋይናንስ አስተዳደርና ሪፖርት የማዘጋጀት ብቃት

11. **ከፕሮጀክቱ የሚጠበቁ ተጨማሪ ጥቅሞች ፤ ውጤቶችና ተጠቃሚዎች፡** ሀ) አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ከፕሮጀክቱ ትግበራ የሚገኝ ጥቅም ይገለጽ ለ) ተጠቃሚዎች እነማን እንደሆኑ ይጠቀሙ

12. **የሚያስፈልግ የገንዘብ ድጋፍና የራስ መቀናጆ ገንዘብ ድርሻ፡** የሚያስፈልግ የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድና የፈጻሚው አካል የመቀናጆ ፈንድ በብር

***<u>ማሳሰቢያ</u>***

***ከ3 ገጽ በላይ ባይሆን ይመረጣል***

***ለወረዳው አገግሮቢግ አስተባባሪ የሚሰጥ***

## አባሪ 2፡ የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳብ መገምገሚያ ቅጽ

**የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ**

(እባክዎትን ሁሉንም ጥያቄዎች ይመልሱ)

1. **ፕሮጀክት ማመልከቻ ቁጥር፡**
2. **የአመልካቹ ስም፡**
3. **የፕሮጀክቱ ርዕስ፡**
4. **ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው፡**
5. **የመመልመያ** መስፈርት፡
   - **ሀ) የእሴት ሰንሰለት የፕሮጀክት ሃሳብ (ጥያቄ ቁጥር 7)** የፕሮጀክት ንድፈ ሃሳቡ አመልካቹ ለመስራት ያሰበውን በድንብ መግለጽ አለበት፡፡ በተመሳሳይ በእሴት ሰንሰለት የተለዩ ችግሮችን ለመፍታት ያለው አግባብነት ይም ብቃት
   - **ለ) የንግድ ልማት እቅድ (ጥያቄ ቁጥር 8)** ሁሉ የፕሮጀክት ሃሳቦች በውስጣቸው ምን አዲስ ነገር አካቶ እንደያዘ፤ አሁን ያለውን ችግር ፕሮጅከቱ እንዴት ሊያሻሽለው እንደሚችል በደነብ መግለፁ፤ የሥራ ዕቅዱ በትግበራ ጊዜ ለቡድኑ ወይም ለጥቃቅን እንትርፕራይዞች ምን ጠቃሚ ነገር እንደሚያስገኝ የሚያሳምን መሆኑ
   - **ሐ) ምን ዓይነት አወነታዊ ተፅዕኖ ሊያመጣ ይችላል (ጥያቄ ቁጥር 11)**የሚገኘው ውጤቱ ሊለካ የሚችል መሆኑ፤ ትግበራው በየምርቱ ላይ ምን እሴት እንደሚጨምር ማመላከት አለበት፤ ለውጡ ዘላቂነት ያለውና አንስተኛ ባለይዞታዎችን የሚጠቅም ስለመሆኑ ያለው ብቃት
   - **መ) የአመልካቹ አቅም** (ጥያቄ ቁጥር 10) ዓላማውን ለማሳካትና በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ድረጅቱ የቴክኒክ፤ የፋይናንስ፤ የአስተዳደር ብቃትና የሰራተኞች ልምድ አንፃር መመዘን አለበት፡፡

| **መስፈርት** | **የመቶኛ ድርሻ (ሀ)** | **በገምጋሚ ከ10 የተሰጠ ነጥብ (ለ)** | **ውጤት ሐ= ሀxለ** |
|---|---|---|---|
| የእሴት ሰንሰለት ፕሮጀክት ሃሳብ | 30% | | |
| የንግድ ልማት ዕቅድ | 30% | | |
| የሚያስከትለው መልካም ተፅዕኖ | 20% | | |
| የአመልካቹ የመፈጸም ብቃት | 20% | | |
| **ድምር** | **100%** | | |

ቀን ______________________________

ገምጋሚ ______________________________

ፊረማ ______________________________

## አባሪ 3፡ የፕሮጀክት ሃሳብ ማቅረቢያ ቅጽ

**የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ**

(እባክዎትን ሁሉንም ጥያቂዎች ይመልሱ)

1. **የአመልካቹ ስምና አድራሻ፡**

2. **ስለ አመልካቹ አጭር መግለጫ** ሀ) ህጋዊ ሰውነት ለ) የተሰማራበት የሥራ መስክ ሐ) በለፉት 3 ዓመታት ያነቀሳቀሰው የሃብት መጠን መ) የያዘው የሰራተኛ ብዛት

3. **ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ፡** ሀ) ስም ለ) በመ/ቤቱ ያለው ሃላፊነት ሐ) አድራሻ መ) ስልክ ቁጥር ሠ) ኢሜል

4. **የፕሮጀክቱ መጠሪያ ስም፡**

5. **ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ (ወረዳ ቀበሌ)፡**

6. **ፕሮጀክቱ የሚተገበርበት ጊዜ፡**

7. **የእሴት ሰንሰለት የፕሮጀክት ሃሳብ፡** የተለዩትን ችግሮች ወይም እጥረቶች ምላሽ በመስጠት ምን ያህል አግባብነት አለው

8. **የንግድ ልማት ዕቅድ፡** የሥራ ዕቅዱ በትግበራ ጊዜ ለቡድኑ ወይም ለጥቃቅን እንተርፕራይዞች ምን ጠቃሚ ነገር እንደሚያስገኝ የሚያሳምን መሆን አለበት፡፡

9. **የሚከናወኑ ተግባራት /የሥራ እቅድ/** ፕሮጀክቱን ለመፈፀም ምን እንደሚሰራ የገለፅ፤ ዝርዝር የሆኑ የሚተገበሩ ሥራዎች የቀመጡ (ደረጃ በደረጃ)፤ መቼ እንደመሰሩ፡ በማን እንደሚከናወን ይገለጽ

10. **ፕሮጀክቱን ለመተግበር ድርጅቱ ያለው ብቃት፡** **ሀ)** ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ሥራ ያለው ልምድ፤ **ለ)** ወደ ሥራ የሚያሰማራቸው ሰራቶኞች የትምህርት ዝግጅት፤ **ሐ)** የፕሮጀክት ፋየናንስ አስተዳደርና ሪፖርት የማዘጋጀት ብቃት

11. **ከፕሮጀክቱ የሚጠበቁ ተጨማሪ ጥቅሞችና ውጤቶች፡** ከፕሮጀክቱ ትግበራ የሚገኙትን ውጤቶች ይገለጹ፤ አሁን ካለው አንፃር ሲመዘን ወደፊተ የሚገኙት ጥቅሞች የገለፁ

12. **ታላሚ ተጠቃሚዎች፡** **ሀ)** የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች እነማን ናቸው **ለ)** ተጠቃሚዎች ስንት ናቸው /ሴት፤ ወንድ **ሐ)** ለአንሰትኛ ባለይዞታዎች የሚያስገኘው ጥቅም ምነድን ነው /ሴት፤ ወንድ/

13. **የበጀት ግምት፡** በሚከተሉት የወጪ ክፍሎች/ምድቦች የሚስፈልገውን የወጪ ግምት ይሙሉ **ሀ)** የሰራተኛ ደመወዝ **ለ)** ሌሎች የዕለት ከዕለት ወጪዎች **ሐ)** የእንቨስትመነት ወጪ **መ)** ጠቅላላ ወጪና የገንዝብ ፍላጎት ሰንጠረዥ ይያያዝ

14. **የፕሮጀክት ፈፃሚው አካል የመቀናጀ በጀት፡** ከፕሮጀክቱ ምን ያህሉን ወጪ በራሱ ገንዘብ

ለመሸፈን ተዘጋጅቷል

---

**15. መለካት የሚችሉ የፕሮጀክት ስኬት አመላካቾች፡** ሁሉንም ሊለኩ የሚችሉ ታላሚ አመላካቾቸች ይገለጹ፤ እንዴትና መቼ እንደሚለኩ ይገለጽ

*ማሳሰቢያ*

***የገጽ ብዛት ገደብ የለውም፡ ሆኖም ግን በተቻለ መጠን ገላጭና መረጃ ሰጪ ስፈላጊ ከሆነም አባሪዎችን ማያያዝ ይቻላል።***

***የፕሮጀክት ሃሰቡ ለወረዳ አግሮቢግ አስተባባሪ የሚሰጥ ይሆናል።***

AgroBIG

## አባሪ 4፡ ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች መከታተያ ሠንጠረዥ

### የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ

ይህ የመከታታያ ሰንጠረዥ በአመልካቹ የሚሞላ ሆኖ ከፕሮጀክት ሃሳቡ ጋር መያያዝ አለበት፡፡

| | የስርዓተ-ፆታ ጉዳች | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | በፕሮክት ዝግጅት፤ ሂደትና በፕሮጀክቱ ሃብት በመወሰን ረገድ ሴቶችና ወንዶች ተሳትፈዋል | | |
| 2 | ከፕሮጀክቱ የሚጠበቀው ጥቅም የሴቶችንና የወንዶችን ፍላጎት፤ ቅደሚያ የሚሰጣቸውንና እጥረቶቻቸውን የሚያሟላ ነው | | |
| 3 | የሴቶችን ችግር የሚፈቱ እርምጃዎች ተካተዋል ( ለምሳሌ በፕሮጀክት ስራ የሚያሳልፉትን ጊዜ መጨር፣ ልጆችን የመከባከብ ሃላፊነት፤የሴቶችን እንቅስቃሴ በመገድብ ረገድ | | |
| 4 | የሴቶችና የወንዶች በእሴት ሰንሰለት ትግበራ የሚወጣ ወጪና የሚገኛው ጥቅም ለየብቻው ተገምቷል (ከጊዜ አንፃር፤ ከጉልበት ዋጋ) | | |
| | **ለ. ከአካባቢ እንክብካቤ አንጻር** | | |
| 5 | ከሮጀክቱ ጋር ተያይዞ የአካባቢ እንክብካቤን ሊቀይር የሚችል ሊመጣ እንደሚችል ታሳቢ ተደርጓል | | |
| 6 | በፕሮጀክቱ ትግበራ የተሰማሩ ሰዎች ከስራው ጋር በተያያዘ የሚለቀቅ ፍሳሽ ቆሻሻ፤ንጥረ ነገር (ኬሚካል፤ ድመፅ፤ ጭስና መጥፎ ሽታ ለማስከተል ምክንያት ሊሆን ይችላል | | |
| 7 | ለከፍተኛ አካባቢ ብክለትና ለጤና የማይመች ምክንያት ሊሆን የሚችልና ስጋቱን ለመቀለበስ የሚያሰቸግር ሁኔታ ይኖራል | | |
| 8 | ፕሮጀክቱ የሚስከትለውን ችግር ለመቀነስ ወይም ለማሰወገድ የሚያስችል አማራጭ ሊኖር ይችላል | | |

## አባሪ 5፡ የፕሮጀክት ሃሳብ መገምገሚያ ቅፅ

**የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ**

1. **ፕሮጀክት ማመልከቻ ቁጥር**
2. **የአመልካቹ ስም**
3. **የፕሮጀክቱ ርዕስ**
4. **ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው**
5. የማወዳደሪያ መስፈርት (ለዝርዝሩ የማኑዋሉን ክፍል 4.5 ይመልከቱ)

| **መስፈርት** | **የተሰጠው ክብደት መቶኛ (ሀ)** | **በገምጋሚው የተሰጠው ነጥብ (ከ10) (ለ)** | **ውጤት ሐ= ሀ x ለ** |
|---|---|---|---|
| ሀ. እሴት ሰንሰለት ፕሮጀክት ሃሳብ | 15% | | |
| ለ. የንግድ ልማት ዕቅድ | 15% | | |
| ሐ. ሊያስከትለው ሚችል አወነታዊ ተጽዕኖ | 10% | | |
| መ. ትግበራ | 10% | | |
| ሠ. የአመልካቹ የመፈጸም ብቃት | | | |
| ረ. ተጨማሪ ጥቅሞች | 10% | | |
| ሰ. ታላሚ ተጠቃሚዎች | 10% | | |
| ሸ. የመቀናጆ በጀት | 10% | | |
| ቀ. ስኬታማ አመላካቾች | 3% | | |
| በ. ሥርዓተ-ፆታ | 7% | | |
| በ. የአካባቢ እንክብካቤ | 5% | | |
| | 100% | | |

| አጠቃላይ ምልከታ |
|---|
| በፕሮጀክት ሃሳቡ ላይ በኢኮኖሚ፤ በማህበራዊና በቴክኒክ ጉዳደ አጠቃላይ አስተያየት መስጠት |

የገምጋሚው ምክረ ሃሳብ

ማደማደሚያ

ሀ. እንዲጸድቅ ማቅረብ

ለ  እንደገና እንዲከለስና  ተመልሶ እንዲመጣ

ሐ. የፕሮጀክት ሃሰቡን ውድቅ ማድረግ

ቀን ________________________________

ገምጋሚው ________________________________

ፊርማ ________________________________

## አባሪ 6 ሕጋዊ የበጀት ድጋፍ የውል ስምምነት ቅፅ

# በኢትዮ-ፊንላንድ ልማት ትብብር የአማራ አግሮቢግ ፕሮገራም

**በአግሮቢግ ፕሮገራምና**

በ ___________________________ ___________________________ መካከል የተፈረመ

**ህጋዊ የውል ሥምምነት**

የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ በአግሮቢግ ፕሮገራም በአማራ ክልል ውሰጥ በኢትዮጵያና በፊንላንድ መንግስታት በተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ የሚተገበር ነው፡፡ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የፕሮገራሙ ህጋዊ ባለቤት ነው፡፡ ቢሮው በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድዩሚከናወኑ ማንኛውንም ተግባር ቢሮውን በመተካት እንዲያከናውን የአግሮቢግ ፕሮገራም ድጋፍ ዩኒትን ወክላሏል፤ የፕሮግራሙ ፀሃፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ይህ ህጋዊ የውል ስምምነት የሁለቱን ተዋዋይ ማለትም የአግሮ ቢግእና የ ___________________

ከዚህ በኋላ የፕሮጀክት ፈፃሚ ተብሎ የሚጠራ በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት የሚጠበቅባቸውን ገዴታ ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት በዝርዝር ይዟል፡፡

1) **የፕሮጀክቱ መጠሪያ ስም፡** ይህ የውል ስምምነት የሚሸፍነው የፕሮጀክት አስፃሚው ከመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ የፋይናንስ ምንጭ ጥያቄ ተከትሎ ለ__________________ (የፕሮጀክቱ መጠሪያ) ፕሮጀከት ማሥፈፀሚያ የሚውል ከአግሮቢግ በተገኘ ድጋፍ ለሚከናወን ተገባራትና በፕሮጀክቱ ሰነድ አባሪ 1 ላይ ለተጠቀሱና ለተፈቀዱ ወጪዎችን የሚያካተት ነው፡፡

2) **የፕሮጀክት አስፈፃሚውን ስለሚወክል ግለሰብ፡** የፕሮጀክት አስፈጻሚው ድርጅት መ/ቤቱን ወክሎ ስለፕሮጀክቱ አሰዳደርና የተለያዩ ግንኙነቶችን የሚያደርግ ሰው ይመድባል፡፡ የተወከለው ሰው የፕሮጀክቱን አፈፃፀም የሚያሳይ ሩብ ዓመታዊ ሪፖርት ለአግሮቢግ የማቅረብ ሃላፊነት አለበት፡፡

3) **የተፈቀደ የድጋፍ ፈንድ መጠን፡** ለዚህ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የተፈቀደው የገነዘብ መጠን በአሃዝ ብር __________________ በፊደል (__________________________________________) ነው፡፡

4) **የአመልካቹ የራስ ወይም የመቀናጀ በጀት ድርሻ፡** ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተፈቀደው በጀት ለፕሮጀክት አሰፈፃሚው ከመከፈሉ በፊት የፕሮጀክቱ የመቀናጀ በጀት ድርሻ በአሃዝ ብር __________________ በፊደል (__________________________________________) ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ ብቻ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር አሰቀድሞ ገቢ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

5) **ስምምንቱ ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ፡** ለፕሮጀክቱ ትግበራ የተፈቃደውን ገንዝብ ይህ ውል በሁለቱ ወገን ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ መጠቀም ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን ከተፈረመበት ቀን በፊት የወጣን ወጪን በዚህ ገንዝብ መተካት ወይም መሸፍን አይቻልም፡፡

6) **የፕሮጀክቱ የቆየታ ጊዜ፡** የፕሮጀክቱ የማጠናቀቂ ጊዜ በፕጀክቱ ሰነድ የተገለፀውና በሁለቱ ወገን ውሉ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ __________ ወር ሆኖ _____ ቀን______ ወር __________ ዓ/ም

ይሆናል። ከውሉ ማጠናቀቂያ ቀን በኋላ የሚወጣ ማንኛውም ወጪ ተቀባይነት አይኖረውም። የፕሮጀክቱን የማጠናቀቂያ ጊዜ ሊራዘም የሚችለው ጥያቄው በጽሁፍ ለአግሮቢግ ቀርቦ ተቀባይነት አግኝቶ ሲፈቀድ ብቻ ይሆናል። የፕሮጀክቱ የማጠናቀቂያ ጊዜን ማራዘም አስፈላጊ ከሆነ የፕሮጀክት አስፈጻሚው ከሁለት ወር በፊት አስቀድሞ ጥያቄውን በፅሁፍ ለአግሮቢግ ማቅረብ ይጠበቅበታል።

7) **እራሱን የቻለ የባንክ ሂሳብ ቁጥር መክፈት፡** የፕሮጀክት አስፈጻሚው ለዚህ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ብቻ የሚውል ከሌላ የፋይናንስ ምንጭ ጋር ሳይቀላቀል ራሱን የቻለ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይከፈታል። አግሮቢግ ለፕሮጀክቱ የሚያስፈለገውን ገንዘብ በዚህ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ያደርጋል። የባንክ ሂሳብ ቁጥሩ ቢያንስ በሁለት ጣምራ ፈራሚዎች የሚንቀሳቀስ መሆን አለበት። የፈራሚዎች የመታወቂያ ወረቀትም ፎቶ ኮፒ ተደርጎ ለአግሮቢግ መላክ አለበት። የፕሮጀክት አስፈፃሚው የተከፈተውን የባንክ ሂሳብ ቁጥር ለፕሮጀክቱ አገልገሎት ብቻ መጠቀም እንዳለበት ተስማምቷል።

8) **የፕሮጀክቱ ገንዘብ አጠያየቅ፡** ለፕሮጀክቱ በየሩብ ዓመቱ የሚያስፈለገው የገንዘብ መጠን (የጥሬ ገንዘብ ፍላጎት) ከፕሮጀክቱ ሰነድ ጋር መየያዝ ይኖርበታል። የፕሮጀክት አስፈጻሚው ከሁለት ሳምንት በፊት ከጥሬገንዘብ ፍላጎት በተቀመጠው መሰረት ለሩብ ዓመቱ የሚያስፈለገውን ገንዘብ (አስፈላጊ ከሆኑ ደጋፊ ሰነዶች ጋር በማያያዝ) አግሮቢግን ይጠይቃል።

9) **ገንዝብ ለመልቀቅ የሚደረግ እንቅስቃሴ፡** የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ያለበት ደረጃ ከተጣራ በሗላ የተጠየቀው ገንዘብ ይለቀቃል። የቀረበው የክፍያ ጥያቄ ተሎ ለመልቀቅ በውሉ መሠረት መሟላት ያለባቸውና በአግባቡ ተያየዘው መቅረብ ባለባቸው ደጋፊ ሰነዶች ጥራት ይወሰናል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጉዳች ሁሉ የወረዳውን የአግሮቢግ አስተባባሪን ማነጋገር ይቻላል።

10) **ገንዝብ ለመልቀቅ ቅደመ ሁኔታዎች፡** አግሮቢግ ገንዘቡን ለፕሮጀክት የሚለቀው በቅደመ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ሲሆን የፕሮጀክት አስፈጻሚው ተቀባይነት ያለው የስራ አፈጻጸም ሪፖረት፤ በፕሮጀክት ሃሰቡ በተገለፀው መሠረት መከናወን ያለበቸው ተግባራት መከናወናቸው፤ በፈንዱ ሴክረታሪያት የሚፈለጉና ተቀባየነት ያለው የሂሳብ ሪፖርት እንዲሁም የባንክ መግለጫዎች ተያይዘው ሲቀርቡ የተጠየቀው ገንዝብ ይለቀቃል።

11) **የአፈፃፀም ሪፖርት፤ ክትትልና የተገኘን ውጤት ማሳወቅ፡** የፕሮጀክት አስፈጻሚው ድርጅት እስከ ፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜ ያለውን የየሩብ ዓመቱን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ለፈንዱ ሴክረታሪያት (አግሮቢግ) ለማቅረብ ተስማምቷል። የፕሮጀክቱ ትግበራን ለመከታተል ሲባል የመቀናጀ ድጋፍ ሂደት በውስጡ የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድን አፈፃፀሙን መገምገምን ሁሉ ያካትታል። ስለሆነም የፕሮጀክት አስፈፃሚው የፋይናንስ ድጋፍ ሰጪው አካል ጥናቶችን ለማስጠናት፤ ፕሮጀክቱን ለመከታተል፤ በተለያዩ አከላላት ለሚዘጋጁ የመስክ ጉብኝቶች (ለመንግስት አካል ወይም የለጋሽ ወኪል)፤ በፕሮጀክቱ የተገኙ ውጤቶችን ለማስተዋወቅ ሲባለ ለሚዘጋጁ ሁሉ ሙሉ ትብብር ለማድረግ ተስማምቷል።

12) **ፕሮጀክትን ማጠናቀቅ፡** በአግሮቢግ ፕሮገራም መመሪያ መሠረት የፕሮጀክት አስፈጻሚው የፕሮጀክተ ቆይታ ጊዜ ጨርሶ ሥራው ሲጠናቀቅ የፕሮጀክቱን የማጠናቀቂያ ሪፖርት የማዘጋጀት ሃላፊነት አለበት። ፕሮጀክቱ አስፈጻሚ የሚጠበቅበትን ሁሉ አሟልቶ ስለማጠናቀቁ የሚገልጽ የፕሮጀክት መዝጊየ ድብዳቤ ከአግሮቢግ/ከሴክረታሪያት ጽ/ቤት እስካለደረሰው ጊዜ ድረስ በፕሮጀክቱ ላይ ያሉ ስምምነቶች ሁሉ ተቀባይነት አላቸው። እነዚህ ከተፈጸሙ በኋላ ያልተከፈለው የመጨረሻ ቀሪ ገንዘብ 5% ይለቀቅለታል።

13) **የፕሮጅክት ገንዘብ መወረስ፤ የካሰ ክፍያና ለማስያዣ አለማዋል፡** የፕሮጀክት አስፈጻሚው የተለቀቀው ገንዝብ ስምምነት በተደረሰበት ተግባር ብቻ ፤ በተመደበው የወጪ ርዕስና በመጨረሻ

ላይ ስምመነት በተደረገበት የፕሮጀክት እቅድ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ተስማምቷል፡፡ በተፈቀደ በጀት ላይ ከአንዱ የወጪ ርዕስ ወደ ሌላ የወጪ ርዕሰ የሚደረግ ሽግሽግ ከበጀት በላይ የወጣን ወጪ ለማስተካከል የሚደረግ ዝውውር ቅድሚያ የአግሮቢግ ስምምነት በጽሁፍ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ የፕሮጀክት አስፈሚው መ/ቤት የፕሮጀክቱን ድጋፍ ፈንድ መውረስ፤ የዕዳ ማካካሻ ማደረግ ወይም ለሦሥተኛ ወገን አሳልፎ ማስተላለፍ አይቻልም፡፡

14) **የማጭበርበር ድርጊት፡** በፕሮጀክቱ ሂደት ወቅት የፕሮጀክት አስፈጻሚው ከዚህ ውል ጋር በተያያዘ የማጭበርበር ተግባር ቢፈጽም ወይም ከላይ የተገለፁትን ማሟላት ቢሳነው፤ የፕሮጀክተ ፈፃሚው ድርጊቱን የፈጸሙትን ግለሰቦች በስም ገላፆ ማሳወቅ፤ አስፈላጊም ከሆነ በብዙሃን መገናኛ በህተመት ወይም በአየር ላይ የማወጣትና ይህም ሲደረግ አግሮቢግን ለዚህ ጉዳይ ተጠያቂ አለመሆኑን ተስማምቷል፡፡ ወንጀሉ ወይም ድርጊቱ በፕሮጀክቱን ሃብት ላይ ብክነት ወይም ምዝበራ ያስከተለ ከሆነ የአግሮቢግ ሴክረታሪያት ሃብቱን ለማስመልስና ለማስተካት ወደ ህግ ሊሄድ ይችላል፡፡ ወንጀል በፈጸሙት አካላት ላይም ክስ የመመስረት መብት አለው፡፡

15) **የፕሮጀክቱን ሂሳብና ሰነዶችን የመመለክት መብት፡** አግሮቢግ የፕሮጀከቱን ውጤትንና ማንኛውንም የፕሮጀክቱን የሂሳብ ሰነዶችና መዛግበትን በየትኛውም ጊዜ የመጎብኘትን የመመልከት መብት አለው፡፡ የፕሮጀክት አስፈፃሚው ያለምንም ገደብ ሁሉንም ሪፖርቶች፤ ሰነዶችና ከውሉ ጋር የተያያዙ ምዝገባዎችን ሁሉ ለማቅረብና ለማሳየት ተስማምቷል፡፡

16) **የፕሮጀክቱን ድጋፍ ፈንድ ስለማስመርመር፡** ይህ ስምምነት ለተደረሰበት ተግባር ማስፈፀሚያ የተሰጠው ገንዘብ የህዝብ ሀብት ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ሃበት ለታለመለት ተግባር በአግባቡ ሥራ ላይ ለመዋሉ በመንግሰት ኦዲተሮች ወይም በሌሎች በሚሰየሙ የሂሳብ መርማሪዎች ኦዲት ይደረጋል፡፡ ሁሉም የሂሳብ መዛግብትና የግዢ ሰነዶች ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ቢያነስ ለ3ዓመት ያህል ለኦዲትና ለአንዳንድ ሥራዎች አመች በሆነ መልኩ ተጠብቀው መቀመጥ አለባቸው፡፡

17) **ኪሳራና ጉዳት፡** የፕሮጀክት አሰፈፃሚው ስምምነት በተደረሰበት ፕሮጀክት ላይ በራሱ ድርሻ የሚጠበቅበትን ለማከናውን ሙሉ መብት አለው፡፡ ከፕሮጀክቱ ጋር በተያያዘ በህይወትም ሆነ በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት አስፈላጊውን የመድን ዋስትና ሽፋን እንዲያገኝ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡ አግሮቢግ ከፕሮጀክቱ ትግበራ ጋር ተያይዞ ለሚመጣ ማንኛውም ጉዳት ሃላፊነት የለበትም፡፡ የፕሮጀክት አስፈጻሚው በአግሮቢግም ሆነ በራሱ ሠራተኞች ላይ ጉዳት እንዳይደርስና ካላስፈላጊ ኪሰራ ለመራቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

18) **አለመግባትን ወይም ግጭትን መፍታት፡** ከፕሮጀክቱ ትግበራ ጋር በተያያዘ አለመግባባት ቢፈጠር የፕሮጀክት አስፈፃሚውና አግሮቢግ ቅራኔውን በመግባባት ለመፈታት ተስማምተዋል፤ ሀኖም ግን በሁለቱ አካላት አለመግባባቱን ለመፈታት ካልቻሉ ጉዳዩ በመንግሰት በኩል ውሰኔ እንዲያገኝ ለገንዘብብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ይቀርባል፡፡

**ወር______ ቀን______ ዓ/ም ባህርዳር ላይ ተፈረመ**

| | |
|---|---|
| <u>አግሮቢግ</u> | <u>የፕሮጀክት አስፈፃሚ</u> |
| ስም | ስም |
| ______________________________ | ______________________________ |
| ሃላፊነተ | ሃላፊነት |
| ______________________________ | ______________________________ |

**<u>ታዛቢዎች</u>**

| <u>*ሥም*</u> | <u>ፊርማ</u> |
|---|---|
| 1. ______________________________ | ______________________________ |
| 2. ______________________________ | ______________________________ |
| 3. ______________________________ | ______________________________ |

*አባሪ 1*

*የተፈቀደ የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ የፕሮጀክት ሃሳብ*

## አባሪ 7፡ የሩብ ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ

**የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ**

ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ ______________________________

የፕሮጀክቱ መለያ ቁጥርና መጠሪያ ስም ______________________________

የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካል ______________________________

ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው

### የሪፖርት አዘገጃጀት

1. **በተመረጡ ምርቶች የእሴት ሰንሰለት ላይ ስላለው አጠቃላይ ሁኔታ ትንታኔ**

   በዚህ ሪፖርት በተደረገበት ወቅት በተመረጡት የእሴት ሰንሰለት ላይ በዋነኛነት የታዩ ለውጦች ምነድን ናቸው? (ለምሳሌ፡ በባለድርሻ አካላት አከባቢ፤ በገበያ፡ በዋጋ፤ በማቀነባበር)

2. **ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ**

   - ግብዓትን ከመጠቀም አንፃር
   - በእቅድ ከተያዘው የተከናወኑ ተግባራት
   - ያልተከናወኑ ተግባራት
   - የተገኘ ውጤትና ያልተሳካ

3. **ውጤትን መፈተሽ /መዳሰስ/**

   - የሩብ ዓመቱ ትግበራ ዋና ግብ ምን ነበር?
   - ግቡ ተሳክቷል? በምን ምክንያት ተሳካ? ያልተሳካ ከሆነ ምክንያት ምን ነበር?
   - ትግበራው በእቅዱ መሰረት እየሄደ ነው? ካልሆነ ምን ማስተካከያ እርምጃ ይወሰድ?
   - በመጪው ሩብ ዓመት የምንጠብቀው ዋናው ውጤት ምንድን ነው?

AgroBIG

## አባሪ 8፡ የፋይናንስ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅፅ

**የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ**

ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ ______________________________

የፕሮጀክቱ መለያ ቁጥርና መጠሪያ ስም ______________________________

የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካል ______________________________

| የፕሮጀክት ክፍሎችና የወጪ ምደቦች መጠሪያ | የወጪ ሂሳብ መደብ | የባለፉት ሩብ ዓመታት ወጪ | የዚህሩብ ዓመት ወጪ | ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት |
|---|---|---|---|---|
| 1. (የፕሮጀክት ክፍል መጠሪያ ስም) | | | | |
| 1.1 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 1.2 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| **ንዑስ ድምር** | | | | |
| 2. (የፕሮጀክት ክፍል መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.1 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.2 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.3 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| **ንዑስ ድምር** | | | | |
| 3. (የፕሮጀክት ክፍል መጠሪያ ስም) | | | | |
| 3.1 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.2 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 2.3 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 3.4 (የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| 3.5(የወጪ ምድብ መጠሪያ ስም) | | | | |
| **ንዑስ ድምር** | | | | |
| **ጠቅላላ ድምር** | | | | |

## አባሪ 9፡ የበጀት ድጋፍ መጠየቂያ ቅፅ

**የመቀናጆ ድጋፍ ፈንድ**

ቀን ________________________________________

ሪፖርቱ የሚሸፍነው ጊዜ ________________________________________

የፕሮጀክቱ መለያ ቁጥርና መጠሪያ ስም ____________________________

የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካል ________________________________________

| | | |
|---|---|---|
| ለፕሮጀክቱ የተፈቀደ በጀት | ብር | |
| ባለፉት ጊዚያት ተጠየቆ የመጣ | ሲቀነስ | |
| ከአግሮቢግ ተጠይቆ ያልመጣ | = | |

| | | |
|---|---|---|
| ከአግሮቢግ የተዛወረ ጠቅላላ የገንዘብ መጠን | ብር | |
| ሲቀነስ፡ ሥራ ላይ የዋለ የወጪ ድምር | ሲቀነስ | |
| በድርጅቱ የሚገኝ ከወጪ ቀሪ | = | |

| | | |
|---|---|---|
| የሚቀጥለው ሩብ ዓመት የወጪ ግምት | ብር | |
| ሲቀነስ፡ በድርጅቱ የሚገኝ ከወጪ ቀሪ | ሲቀነስ | |
| ከአግሮቢግ ለሚቀጥለው ምላክ ያለበት | = | |
| | | |
| **የማመሳከሪያ ዝርዝር** | አዎ | አይደለም |
| የባለፈው ሩብ ዓመት የፋይናንስ ሪፖርት ተያይዟል? | | |
| የሩብ ዓመቱ መጨረሻ የባንክ መግለጫ ተያይዟል? | | |
| የሩብ ዓመቱ መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ሚዛን ማረጋገጫ ተያይዟል? /ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ/ | | |
| የባንክና የጥሬ ገንዘብ ሚዛን ከድርጅቱ ከወጪ ቀሪ ጋር ተመሳሳይ ነው? | | |
| የፕሮጀክቱ የሩብ ዓመት ክንውን ሪፖርት ተያይዟል? | | |
| የሚቀጥለው ሩብ ዓመት የወጪ ግምት በገልጽ ተዘዳጅቶ ተያይዟል? | | |

ፊርማ

የመ/ቤቱ ሃላፊ/ተወካይ ስም

## <u>*አባሪ 10፡ የፕሮጀክት ማጠናቀሪያ ሪፖርት ቅፅ*</u>

***የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ***

የፕሮጀክት ትግበራ የሚሸፍነው ጊዜ ______________________________

የፕሮጀክቱ መለያ ቁጥርና መጠሪያ ስም______________________________

የፕሮጀክቱ ፈጻሚ አካል______________________________

ድርጅቱን ወክሎ ግንኙነት የሚያደርግ ሰው ______________________________

### የሪፖርት አዘገጃጀት

1. **በተመረጡ ምርቶች የእሴት ሰንሰለት ላይ ስላለው አጠቃላይ ሁኔታ ትንታኔ**

   - በዚህ ሪፖርት በተደረገበት ወቅት በተመረጡት የእሴት ሰንሰለት ላይ በዋነኛነት የታዩ ለውጦች ምንድን ናቸው? (ለምሳሌ፡ በባለድርሻ አካላት አከባቢ፤ በገበያ፡ በመሸጫ ዋጋ፤ በማቀነባበር
   - የፕሮጀክቱ ፈጠራ፤ የተቀመጠው መፍትሄ፤ ገለፃ በዋጋ ሰንሰለት ላይ ምን ያህል ተፅእኖ አሳድሯል?

2. **ፕሮጀክቱ ያለበት ደረጃ**

   - ግብዓትን ከመጠቀም አንፃር
   - የተሳታፊ ብዛት /ሴት/ወንድ
   - በእቅድ ከተያዘው የተከናወኑ ተግባራት ፤ያልተከናወኑ ተግባራት
   - የተገኘ ውጤትና ያልተሳካ

3. **ውጤትን መፈተሽ /መዳሰስ/**

   - የፕሮጀክቱ ግብ ምን ነበር?
   - ግቡ ተሳክቷል? በምን ምክንያት ተሳከካ? ካልተሳካ ምክንያት ምን ነበር?
   - የፕሮጀክቱ ታላሚዎች ከትገበራው መጠቀም ጀምረዋል?

4. **የፕሮጀክቱ ዘላቂነትን በሌሎች አካለት መዛመት**

   - ይህ ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ በኋላ ይቀጥላል? የሚቀጥል ከሆነ በምን የፋይናንስ ምንጭ ወደ ሊሌች አካባቢ ተዛምቶ ሊቀጠል ይችላል?
   - ወደ ሌሎች አካባቢ የሚዛመት ከሆነ በምን መልኩ ሊሳካ ይችላል?

*አባሪ*

*የሂሳብ ሪፖርት*

1. *ስምምነት ተተደረሰባቸው የውጤተ አመላካቾችና የሚመዘኑ ውጤቶች*

AgroBIG

## አባሪ 11፡ የቡድን ተኮር ማወያያ ቅፅ

**የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ**

ከፕሮጀክቱ ትግበራ መጨረሻ ላይ ከተወሰኑና ከሚመለከታቸው ቁልፍ ባለድርሻ አካለት ጋር ቡድን ተኮር ስበሰባ የሚደረግ ሲሆን ዓላማውም ስለፕሮጀክቱ ውጤት ለመወያየትና ለመገምገም ነው፡፡ የዚህ ዓይነት ውይይት የባለድረሻ ካላትን ልምድ ለማወቅ መልልካም አጋጣሚ ነው፡፡ ለቡድን ተኮር ውይይት የሚጠሩ ተሳታፊዎች በተቻለ መጠን የሴቶች ተሳትፎ ተመጣጣኝ መሆኑንና ሁሉም አባላት ሃሳባቸውን ያለችግር እንዲገልፁ የሚያበረታታ መሆን አለበት፡፡

የቡድን ተኮር ውይይቱ በ3 ጉዳች ላይ ያተኩራል፡፡

1. **ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካቾች**

   የፕሮጀክቱ ዓላማ ምን ነበር? ፕሮጀክቱ ዓለማውን አሳክቷል ወይስ አልተሳካም? ለውጤታማነቱ ወይም ላለመሳካቱ ምክንያቶች ምን ነበሩ?

   የፕሮጀክቱ አዲስ ፈጠራ ገፅታ ምንድን ነው? እንደታሰበው ሥራ ላይ ውሏል? ለታላሚዎች /ሴቶችና ወዶች/ ከፕሮጀክቱ ምን ጥቅም አገኙ?

   የቡድን ተኮር ተወያዮች በፕሮጀክቱ ምክንያት በኑሯቸው ላይ መሰረታዊ የሆነ የገቢ መጨመር፤ የምርት ማደግ፤ የተሸለ የመሸጫ ዋጋ ማገኘት፤ሌሎች ተጨባጭ መፍተሄዎች ተመለክተዋል?

2. **ለፕሮጀክቱ ታላሚዎች ተጨባጭ የታየ ለውጥ**

   - የአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ በውይይቱ ወቅት ከተሳታፊዎች ምን መሰረታዊና ተጨባጭ ለውጥ እንዳገኙ መለየት ይኖርበታል፡፡
   - ከውይይታቸው በፊት የተወሰኑ ተሳታፊዎች ቃለምልልስ (በአባሪ 12 መሠረት) ያደርጋሉ፡፡ የአግሮቢግ ወረዳ አስተባባሪ የተደረገው ቃለምልልስ የሁሉንም ገበሬዎች ሃሳብ የሚወክል ስለመሆኑ አወያይቶ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ ለምሳሌ የታየው የምርት መጨመር ለተወሰኑ የቡድን አባላት ወይስ ለሁሉም ስለመሆኑ (ሴት/ወንድ ለያይቶ ማየት ይቻላል)፡፡

3. **ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች ላይ መወያየት**

   የመቀናጀ ድጋፍ ፕሮጀክቶች መነሻቸው የተለያየ ቢሆነም በሁሉም ላይ ፈርጀ ብዙ ጉዳች በውል መመልከት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የሚደረገው ውይይቱ ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች መከታተያ ቅጽ አባሪ 4 መሰርት ይሆናል፡፡ የወረዳው አግሮቢግ አሰተባባሪ እንደአመቻችነቱ በቡድኑ ውይይት ወቅት የተደረሰባቸውን የማደማደሚያ ሃሳቦች ሪፖርት ማደረጉ አስፈላጊ ነው፡፡ የተሞላው የመከታተያ ቅጽ ለፈንዱ ሴክረታሪያት ከሚላከው ሪፖርት እነዲሁም በአንዳንድ በጣም ጠቃሚ በሆኑ ግኝቶች ላይ ከነማብራሪው ተያይዞ ይላካል፡፡

አባሪ 12፡ የተጠቃሚዎችን መስክርነት ማሰባሰብ ቅፅ

**የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ**

አንድ የፕሮጀክት ተጠቃሚ አርሶአደር በሕይወቱ ያገኘውን ለውጥ ለሌላው የምስክረነት ቃሉን የሚሰጥበት ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነት መረጃዎችን መሰብሰብ አርሶአደሮች ሃሳባቸውን በግለጽ ለመግለፅ የረዳቸዋል፡፡ ዋናው ቁም ነገርና መተኮር ያለበት ጉዳይ ከፕሮጀክቱ ጋር ተያይዞ ምን ተግባር እንደተከናወነ፤ ምን ውጤት እንዳገኘ ያለውን ስሜት ማወቅ ነው፡፡

ይህም የፕሮጀክቱን አፈጻፀም አሳታፊ በሆነ መልኩ ለመገምገምና ትምህርት ለመውሰድ ያግዛል፡፡ የዚህ ዓይነት መረጃ የተገኘውን ውጤት አጋኖ እንዳይነገር ከማደረጉም በላይ ከባለቤቱ በቀጥታ ትክክለኛውን መረጃ የሚገኝበት ዘዴ ነው፡፡ የታሪኩ ጸሃፊ አርሶአደሩ ለምን በሕይወቱ ላይ ጥሩ ለውጥ እንደመጣ፤ ወይም ያልጠቀመው እንደሆነ፤ ወይም ምንም ለውጥ እንዳልመጣ ከገለፀ ለምን እነዚህ ከስተቶች እንዳጋጠሙት ምክንያቱን አካቶ መፃፍ አለበት፡፡

**የወረዳው አስተባባሪ በመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ላይ** በአንድ ፕሮጀክት ላይ ቢያንስ 2 ታሪክ (አንድ ሴትና ሌላ አንድ ወንድ) መጻፍ አለበት፡፡

**ዓላማውም ከዚህ በታች የተመለከቱትን መረጃዎች ለማሰባሰብ ነው**

ሀ. ከፕሮጀክቱ ትግበራ በፊት የነበረውን ሁኔታ ለማወቅ (መነሻ መረጃ)

ለ. በትግበራ ወቅት ምን እንደተፈጠረ (የተከናወኑ ተግባራትን የተገኙ ውጤቶች)

ሐ. ከትግበራ በኂላ በተጠቃሚዎች ላይ ምን መሰረታዊ የሆነ ለውጥ እንደመጣ (የፕሮጀክቱ አሰተዋጽዖ)

**ትረካውን ለመፃፍ ሦስት ደረጃዎች አሉት**

1. መሰረታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ
2. ቃለ-መጠይቅ ማድረግና ፎቶግራፍ መውሰድ
3. ትረካውን መፃፍ

**ሂደት 1. መሰረታዊ መረጃዎችን መሰብሰብ**

1. የአርሶ አደሩ ስም፤ ዕድሜ፤ ፆታ፤ የቤተሰብ ሁኔታ፤ የልጅ ብዛት
2. የሚወክለው የህበረተሰብ ክፍል (መሪ፤ ተመሪ፤ ድሃ፤ መካከለኛ፤)

3. የሚያመርተው ምርት ገበያ ተኮር ወይስ የምግበ ሰብል (የት አካባቢ)

4. ሌሎች የማምረቻ መሳሪያዎች (በክበት ፤ የውሃ ማሳቢያ ሞተር)

5. በፕሮጀክቱ ስንት አርሶ አደሮች ተሳታፊ ነበሩ

6. ከፕሮጀክቱ ምን ያህል አርሶ አደሮች (በመቶኛ) ተመሳሳይ ልምድን ውጤት አግኝተዋል?

**ሂደት 2. የቃለ-መጠይቅ አጠቃላይ ይዘት**

7. ፕሮጀክቱ ምን ለማከናወን ነበር የሞከረው?

8. አርሶ አደሮች በፕሮጀክቱ ትግበራ ላይ እንዴትና ለምን ተሳተፉ?

9. ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ ከ1 ዓመት በፊት አርሶ አደሩ ሕይወት ምን የመስል ነበር?

10. በአሁኑ ስዓት ምን የተለየ ነገር አለ? ለአርሶ አደሮች የተለያዩ አገልግሎቶችን በማቅረብ፤ በሰብል ምርትና በግብይት፤ በተለያዩ የገበሬዎች አደረጃጀት

11 በፕሮጀክቱ ምክንያት ለተጠቃሚዎች የመጣው ትልቅ ለውጥ ምንድን ነው?

12. የአርሶ አደሮች ገቢያቸው አድጓል? የገኙትን ገንዘብ እንዴት እየተተቀሙበት ነው?

13. ፎቶገራፋቸውን ለመውሰድ ፈቃድ መጠየቅ ከተቻለም ከግብርና ስራቸው ጋር የተያያዘ ፎቶግራፍ ወይም ካፈሩት ቋሚ ንብረት ጋር ቢሆን ይመረጣል፡፡

**ሂደት 3 ታሪኩን መፃፍ**

ሀ. ከታሪኩ ጋር የሚስማማ አጭርና ገላጭ ርዕስ መሰጠት

ለ. ቃለ-ምልልስ ባደረገው /ችው ግለስብ መሰረታዊ መረጃ መጀመር

ሐ. ትረካው በተቻለ መጠን

- ከፕሮጀክት ትግበራ በፊት የነበረውን (መነሻ መረጃ)
- በፕሮጀክቱ የተከናወኑና የተገቶች ውጤቶች
- በአርሶ አደሩ ሕይወት ላይ የፈጠረው ልዩነት

መ. ታሪኩ በአማርኛ ወይም በእግሊዘኛ እስከ 3 ገጽ ሊሆን ይችላል፡፡ ትረካው በአማርኛ ከሆነ የፈነዱ ሴክረታሪያት ለመረጃ ሲባል ወደ እንግሊዘኛ ይመለሳል

ሠ. ከፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርት ጋር ቢያነስ 2 ትረካዎችን / ፎቶገራፎችን/ በማያያዝ በኢሜል ለፈነዱ ሴክረታሪያት መላክ ይኖርበታል፡፡